የዩሂማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# አንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት( በ2015ዓ.ም በቤንሻንጉል ክልል ትምህርት ቢሮ የታተመ)

በ

ሰይድ አሊ ይመር

ነሀሴ/2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# አንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት (በ2015 ዓ.ም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ የታተመ)

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለ ዩሂማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፤ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ሰይድ አሊ ይመር

አማካሪ ፡-አቶ ደረጀ ገብሬ

ነሀሴ/2016 ዓ.ም/

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለሂውማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት ፣የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን የአማርኛ ቋንቋ ስነ -
ፅሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

## አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ተተኳሪነት (በ 2015 ዓ.ም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ የታተመ)

በ

ሰይድ አሊ ይመር

ነሀሴ /2016ዓ/ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ---------------- ፊርማ------------------

ፈታኝ------------------ ፊርማ------------------

ፈታኝ------------------- ፊርማ-----------------

# ማውጫ

ርዕስ

. ገፅ

ምስጋና ....................................................................................................... i

አጠቃሎ ....................................................................................................... 11

ምዕራፍ አንድ:-መግቢያ ....................................................................................... 2

1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................... 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................................................... 6

1.3 የጥናቱ ዓላማ ....................................................................................................... 12

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................................... 12

1.5 የጥናቱ ወሰን............................................................................................................................................12

1.6 የጥናቱ ውስንነት.......................................................Error! Bookmark not defined.

1.7 የቁልፍ ቃላት ብያኔ ............................................................................................................12

ምዕራፍ ሁለት:-ክለሳ ድርሳናት ....................................................................................... 14

2.1 የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ....................................................................................... 14

2.1.1 መርሃ ትምህርት ....................................................................................... 14

2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት ....................................................................................... 15

2.1.3 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህሪያት ....................................................................................... 16

2.1.4 የመማሪያ መጽሐፍት ይዘትና አዘገጃጀት ....................................................................................... 17

2.1.5 የቋንቋ ክሂሎች አዋህዶ ማቅረብ ....................................................................................... 17

2.2 የማንበብ ምንነት ....................................................................................... 18

2.3 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ....................................................................................... 19

2.3.1 ቅድመ ንባብ ተግባራት ....................................................................................... 19

2.3.2 የንባብ ተግባራት ....................................................................................... 20

2.3.3 ድህረ ንባብ ተግባራት ....................................................................................... 20

2.4 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ......................................................................................21
2.5 የመፃፍ ክሂል ምንነት....................................................................................................22
2.6 የመፃፍ ችሎታን ማዳበር ...............................................................................................24
2.7 የማንበብ እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅት……………………………………………………………………………...24
2.8. የቀደምት ስራዎች ቅኝት.............................................................................................26
ምዕራፍ ሦስት:-የጥናቱ ዘዴ .............................................................................................30
3.1 የጥናቱ ንድፍ ............................................................................................................30
3.2. የጥናቱ አቀራረብ .......................................................................................................30
3.3. የጥናታዊ ዕሁፉ የመረጃ ምንጮች ................................................................................31
3.4. ናሙና አመራረጥ ......................................................................................................31
3.4.1 የጥናቱ ክልል አመራረጥ ..........................................................................................31
3.4.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ……………………………………………………………………………….31
3.4.3 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ …………………………………………………………….....32
3.4.4 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን አመራረጥ ……………………………………………....32
3.4.4.1 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ዳራ ……………………………………………......32
3.5. የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴዎች/መሳሪያዎች ……………………………………….…..34
3.5.1 ሰነድ ፍተሻ ………………………………………………………………………………………..……..33
3.5.2 ቃለ መጠይቅ ……………………………………………………………………………...….33
3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ …………………………………………………………………………………………..34
ምዕራፍ አራት:- የመረጃ ትንተና ......................................................................................36

4.1 የመማርያ መፅሐፉያካተታቸው ዋና እና ንዑስ ርዕሶች.....................................36

4.2 ለአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡ ጥያቄዎች ዓይነት.................................... 38

4.3 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የትእዛዞች አቀራረብ ትንተና....................................................................................................39

4.4 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና ........40

4.5 በመፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የቀረበ የይዘት ትንተና ...................................42

4.6 በመፅሐፉ ውስጥ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች .......................................48

4.7 በመፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳትና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ትንተና..........................................................................................50

4.8 አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የቀረቡት/የተዘጋጁት/ ምንባቦች ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋ ግልፅነት ሁኔታ ..................................................................55

4.9 አንብቦ መረዳት እና ፅህፍትን አቀናጅቶ ለማስተማር የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ ሁኔታ .........................................................................................................55

4.10. በመምህሩ መምሪያ መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አዋህዶ ለማስተማር አቅጣጫ የማሳየት ሁኔታ ቢሆን.....................................................56

4.11 የተማሪው መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂልን አዋህዶ መልመጃዎችን የማቅረብ ሁኔታ ...........................................................................................................................57

ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ እና መፍትሄ ሃሳቦች ..........................................................60

5.1 ማጠቃለያ.................................................................................................60

5.2 **የጥናቱ ግኝት** ...............................................................................................60

5.3 የመፍትሔ ሐሳብ.........................................................................................62

ዋቢ መፃህፍት ...............................................................................................................64

አባሪ አንድ ...............................................................................................................67

**አባሪ ሁለት**

………........................................................................................................................... 67

አባሪ ሦስት ........................................................................................................ 68

አባሪ አራት ........................................................................................................ 69

አባሪ አምስት…………………………………………………………………….....70

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ:-የመማሪያ መፅሀፉ በውስጡ የያዛቸው አብይ እና ንዑስ ርዕሶች………..36
ሰንጠረዥ ሁለት :-በመፅሃፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ተዘጋጅተው የቀረቡ ጥያቄዎች…..38
ሰንጠረዥ ሶስት ፦አንብቦ መረዳት ለማስተማር መልመጃዎችን ለመስራት የትእዛዞች ሁኔታ ትንተና…………………………………………………………………………………..……..…39
ሰንጠረዥ አራት፡-በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተማሪው መፅሐፍ ያሉ ምዕራፎች ስንት ክፍለ ጊዜ እንዳለባቸው የሚታይ ሰንጠረዥ …………………………………………..55

## የአባሪ ማውጫ


የአባሪ አንድ:-የአንብቦ መረዳት ለማስተማር ከቀረቡ ትዕዛዞች መልመጃዎች በምን ሁኔታ እንደሚሰሩ የማይልፁ ትዕዛዝ..........................................................................................39

አባሪ ሁለት:-የፅህፈት ክሂል ለማስተማር የመልመጃዎች ትዕዛዝ......…...............................40

አባሪ ሦስት:-አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ትዕዛዝ ሁኔታ..........................................................................................................................50

አባሪ አራት:-አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የቋንቋ ግልፅ የሌላቸው ቃላት.........................................................................54

አባሪ አምስት:-አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የመምሪያ አቀራረብ ሁኔታ ………………………………………………………………………………………………5
4

# ምስጋና

ይህ የምርምር ስራዬ  ለስኬት እንዲደርስ የእሱ ፍቃድ በመሆኑ ለአላህ ሹኩር(ምስጋና) ይገባው፡፡‹‹ሰው ያስባል በአላህ ይፈፀማል›› እንደሚባለው ስራው በተሳካ ሁኔታ ስላለቀልኝ አልሀምዱሊላህ እላለሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ከጥናቱ ርዕስ ጀምሮ  ግድፈቶችን በማስተካከል እና ደጋግሞ  በማረም የረዱኝ አማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ ምስጋናዬን ከልብ አቀርባለሁ፡፡

በሌላ በኩል ለዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ተተኳሪ ለነበረው አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍ በሶፍት ኮፒ በመስጠት ለተባበሩኝ የማንዱራ ወረዳ ት/ጽ/ቤት ምስጋና ይገባቸው እላለሁ፡

የፅህፈት መሳሪያዎችን፣የምክር አገለግሎት ለሰጡኝ የማንዱራ 2ኛ እና መሰናዶ ት/ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን ላደረጋችሁልኝ እገዛ ፈጣሪ ይክፈላችሁ፡፡

ከዚህ ባሻገር ጥናታዊ ፅሑፌን ከሶፍት ኮፒ ወደ ወረቀት በመቀየር አዘጋጅተው ለአማካሪየ ላቀረቡልኝ ልጆቼ ፀሐይነው መውደዱ እና ለፋጡማ ሰይድ ምስጋናየ ወደር የለውም እላለሁ፡፡የጥናቱን ወጭ በመሸፈን ላስተማረኝ እና ለረዳኝ የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ በጣም አመሰግናለሁ ፡፡

በመጨረሻም የሞራል፣የገንዘብ፣የቤተሰብ ኃላፊነት በመሸከም ርዳታ ላደረገችልኝ ባለቤቴ ለወ/ሮ ዘይነባ ፍሰሀ የስራሽን ዋጋ አላህ ይክፈልሽ እላለሁ፡፡

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ ዋና ዓላማው በ2015 ዓ/ም ታትሞ በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መፈተሽ በ8ኛ ፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ተተኳሪ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም በሰነድ ፍተሻ እና በቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልና የአንብቦ መረዳት ክሂልን አዋህዶ ይዘቶችንና መልመጃዎችን መቅረባቸውና አለመቅረባቸው መመርመር ፤የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦች የቋንቋ ግልፅነት ማየትና ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡትን መልመጃዎች ግልፅነት መመርመር ነው፡፡ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ከፍፃሜ ለማድረስ አጥኚው የተጠቀመ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች መጠናዊ የምርምር ዘዴ እና ዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶች አቀራረብ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ ልምምድ አመቺ መሆናቸውን፤ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፤የመማሪያ መጽሀፉ አቀራረብ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በተቀናጀ መልኩ እንደተዘጋጁና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር እገዛ እንዳላቸው ጥናቱ ፍተሻ አድርጓል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መጨረሻ ውጤት የሚያሳየው የአንብቦ መረዳት እና ለፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ቋንቋውን እንደሚረዱት ሆኖ ቀርቧል፡፡ቢሆንም የተወሰኑ ይዘቶች እና መልመጃዎች የቋንቋ ግልፅነት የሌላቸው መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመጨረሻም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚሰጠው ማሻሻያ ሃሳብ ፤ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በፅሁፍ ለመግለፅ ይዘቶች እና መልመጃዎች በሰፊው ቢዘጋጅ እና ተቀናጅተው ቢቀርቡ፡፡ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች የሃሳብ ግልፅነት የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ ፤ምንባቦች ተሻሽላው ቢቀርቡ በማለት ጥናታዊ ፅሁፍ የመፍትሔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡*

## ምዕራፍ አንድ:-መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች እየተማሩት ባለው ቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት በማዳበር እንዲግባቡበት ማድረግ ነው፡፡ይህን ለማድረግ ደግሞ የመማሪያ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለ ቋንቋ ትምህርት ሲነሳ ቁልፉን ቦታ የሚይዙት የመማሪያ መሳሪያዎች መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ጥናታቸውን ያደረጉ ተመራማሪዎች Grant (1987)፣ Cunnings worth (1995) እና Richads (2001)ገልጸዋል፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የምንላቸው ስርዓተ ትምህርት፣መርሃ ትምህርት፣የተማሪው መማሪያ መጽሀፍና የመምህሩን መምሪያ ያጠቃልላል፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች የቋንቋን ትምህርት ሂደት የተሳካ እንዲሆን የሚያግዙ የትምህርት መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ማንበብ ከፅሁፍ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ መቻል ነው፡፡ Harmer (1991) እንደሚገልፁት፣ ማንበብ በዐይንና በአዕምሮ የሚከናወን ተግባር ነው፤ ዐይን ከተፃፈው ፅሁፍ መልዕክትን ማየት ሲያስችል፣ አዕምሮ ደግሞ ዐይን ያየውን መልዕክት በመገንዘብ ትርጉም ይሰጣል፤ ምላሽም ያዘጋጃል፡፡ በዚህም ማንበብ የተፃፈን ፅሁፍ መልዕክት ማየት ብቻ ሳይሆን፣ በጽሑፍ ውስጥ የሰፈረውን መልዕክት መረዳት ዋና የማንበብ ተግባር ነው፡፡ Khezrlou (2012) እንደሚገልፁትም፣ ማንበብ የተፃፈን ነገር ከዳር እስከዳር ማዳረስ ሳይሆን፣ ማጤንን፣ ማስተዋልንና መመርመርን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ስነልሳናዊና አዕምሯዊ የሆኑ ውስብስብ ነገሮችን አዋህዶ የያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ማንበብ በፀሀፊውና በአንባቢው መካከል የሚደረግ ተግባቦት ነው፡፡ ይህም ፀሀፊው ሀሳቡንና መረጃውን በፅሁፍ ያሰፍራል፤ አንባቢው ደግሞ በፅሁፍ ውስጥ የሰፈሩትን መረጃዎች ይቀበላል (Yaman & Cakici, 2013)፡፡ ይህን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ Yussof, et al (2012) ንባብ ፀሀፊውንና አንባቢውን የሚያገናኝ የተግባቦት መንገድ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይም ማንበብ አዕምሯዊና ማህበራዊ ተግባራት አቀናጅቶ የያዘ በመሆኑ ማገናዘብን፣ ማስታወስን፣ ማመሳሰልን፣ ማጠቃለልን፣ ትኩረት መስጠትንና መገምገምን ስለሚያጠቃልል በትምህርት ሊዳብር ይገባል፡፡

የማንበብ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ቁልፍ ጉዳይ ነው (Duke & Pearson, 2009)፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን መጋቢው (2009) ሲገልፁት፣ በፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ አዳዲስ

መረጃዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሀሳበቸውን መገንዘብ መቻል ነው፡፡ እንዲሁም አንብቦ መረዳት አእምሯዊ ሂደቶችን በማለፍ የሚዳብር ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት በፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ወይም መረዳት ሲሆን የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል (Griffiths & Cansiz, 2015; Ur, 1996; Yaman & Cakici, 2013)፡፡ ሙሉገበያ (2009) አንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ አዕምሯዊ ዕውቀትና ስነልሳናዊ ችሎታ በማጣመር ለፅሁፉ ትርጉም መስጠት፣ ዐውዳዊና ከዐውድ ውጭ የሆኑ ፍችዎችን መገንዘብን ያጠቃልላል፡፡ አንብቦ መረዳት አዕምሯዊ ክዋኔ ብቻ ሳይሆን ስሜታዊ ተግባር ጭምር ነው፡፡ ተማሪዎች ለሚያነቡት ነገር ስሜት የሚሰጡት በማንበብ ክዋኔያቸው የሚከሰቱ አዕምሯዊና ስሜታዊ ተግባር ጥምረት በመሆኑ የማንበብ ተነሳሽነት ማጣት ለአንብቦ መረዳት መሰናክል ነው፡፡

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በ2015 ዓ.ም የታተመው የ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሀፍ ላይ ሲሆን ፤መፅሀፉ አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መተንተን ነው፡፡ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ የሥርዓተ ትምህርት ንድፍ የተነደፈው የአንብቦ መረዳት ና የመፃፍ ክሂሎችን በማካተት ለሁለቱም ክሂሎች እድገት ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ዓለማየሁ (2015) ውጤታማ የቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ምንባቦች ጽሑፍ ክሂሎችን ጋር ማካተት እንዳለበት አበክሮ ይናገራል፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች አንድን ትረካ ወይም መረጃ ሰጭ ጽሁፍ ማንበብ እና ከዚያም ድርሰቶችን ወይም የፈጠራ ምላሾችን በማንበባቸው ላይ መፃፍ ይችላሉ፡፡ ይህ አካሄድ ተማሪዎች የመረዳት ችሎታቸውን በፅሁፍ ተግባራቸው ላይ እንዲተገብሩ ይረዳቸዋል፣ ይህ ደግሞ ግንዛቤን ያጠናክራል፡፡

ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር የማስተማሪያ ስልቶች ወሳኝ ነው፡፡ ባንቴ (2017) ማንበብና መጻፍን ለማዋሃድ የማስተማሪያ ስልቶች ወሳኝ መሆናቸውን አመልክቷል፡፡ መምህራን የማስተማሪያ ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ዕድሎች ይፈጥራሉ ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ምንባብ ካነበቡ በኋላ፣ ተማሪዎች ቁልፍ ጭብጦችን ወይም ክርክሮችን እንዴት እንደሚለዩ እና ከዚያም እነዚህን አካላት በራሳቸው የጽሁፍ ስራዎች እንዴት እንደሚጠቀሙ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ እንደ የአቻ ግምገማዎች ያሉ የትብብር የመማር ስልቶች መጠቀም ተማሪዎች የማንበብ እና የመፃፍ ክሂሎች ላይ አስተያየት እንዲሰጣቸው

በማድረግ እና እርማት በማካሄድ  አስተያየቶችንና እርማትን በማዋሃድ ክሂሎችን እንያዳብሩ ይረዷቸዋል፡፡

የማንበብ ክህሎት ማዳበር ከመፃፍ ክሂል ጋር  የተሳሰረ ነው፡፡ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂሎች ላይ ሲሳተፉ፣ የመረዳት እና የመተንተን ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡ ደረጀ ገብሬ (2018) ለተለያዩ ጽሑፎች የማንበብ እድል ሲኖራቸው ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም እና የተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶችን ግንዛቤ ና የመፃፍ ክሂሎችን እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል፣ ከዚያም በራሳቸው ጽሑፍ ውስጥ ሊተገበሩቸው ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የትረካ ጽሑፎች ማንበብ ተማሪዎች ስለ ትረካ አወቃቀሮች እንዲያውቁ እድል ይፈጥርላቸዋል እና እነዚህን ቴክኒኮች በራሳቸው የመፃፍ ሂደት  ውስጥ እንዲተገበሩ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር  የመጻፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች ከንባብ የቀሰሙትን የታሪክ አወቃቀር ፣ ይዘት አቀራረብ፣ቅደም ተከተል ፣ የሃሳብ አደረጃጀት በራሳቸው የመፃፍ ስራ ላይ ጥቅም ላይ ሲያውሉት ነው፡፡ ተክሌ (2020) አገላለፅ የአፃፃፍ ክህሎት የሚዳበረው ተማሪዎች ከንባብ ያገኙትን ግንዛቤ እንዲተገብሩ በሚጠይቁ ተግባራት በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ሲካተት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ወሳኝ ትንታኔን የሚያካትቱ መልመጃዎች መፅሀፍ ውስጥ መካተታቸው መፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር ወይም ተማሪዎችን የፈጠራ ምላሾች እንዲለማመዱ እና የአጻጻፍ ብቃታቸውን እንዲያጠሩ ያግዛቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ ያነበበውን ፅሁፍ ግምገማ ሊጽፍ ይችላል፣ በምንባብ ውስጥ  ያለውን መረጃ ተጠቅመው  በፅሁፍ ትንታኔያቸው ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የመፃፍ ክሂል  ከማሳደጉም በላይ ስለ ንባብና ጽሑፉ ያላቸውን ግንዛቤ ያሰፋዋል፡፡

በቅንጅት የይዘት አቀራረብ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር  የግምገማ እና ግብረመልስ ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ የተቀናጀ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂልን ለመገምገም ውጤታማ የግምገማ ግብረመልሶችና ልምዶች አስፈላጊ ናቸው፡፡ መኮንን (2019) ምዘናዎች የማንበብ እና የመጻፍ ብቃቶችን ለመለካት መቅረጽ እንዳለባቸው አጉልቶ ያሳያል፡፡ ምንባቦችን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችና ምዘናዎች የተማሪዎችን ችሎታ የመላካት ዕድል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም በግምገማ የተገኘው አስተያየት ከንባብ የተካተቱ ይዘቶችን እና የአጻጻፍ ጥራትን

የሚያጎለብቱ ሆነው መቅረብ አላባቸው፡፡ ገንቢ ግብረመልስ ተማሪዎች የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታቸውን እንዴት በሚገባ እንደሚያዋህዱ እና የት መሻሻል ማድረግ እንደሚገባቸው ቦታውን እንዲለዩ እና እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡

የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታዎች ለማዳበር ባህላዊ እና አውዳዊ አግባብነት ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ማለት የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታዎች ውህደት ለመፍጠር ባህላዊ እና በዐውደ-ጽሑፉ ጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው ፡፡ እንደ ዓለማየሁ (2015) የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና የአገር ውስጥ ባህልን የሚያንፀባርቁ ጽሑፎችን ማካተት ለተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ሥራዎችን የበለጠ ትርጉም ያለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፣ የሀገር ውስጥ ተረት ወይም ታሪካዊ ፅሁፎችን እንደ የንባብ መሳሪዎች እና የፅሁፍ ማበረታቻዎች በመጠቀም ተማሪዎች ከይዘቱ ጋር በጥልቀት እንዲገናኙ እና የማንበብ ችሎታቸውን በራሳቸው የባህል አውድ ውስጥ እንዲመለከቱ ያግዛቸዋል፡፡

አንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ተግባራዊ ለማድረግ የመምህራን ስልጠና እና ሙያዊ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ የንባብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማዋሃድ በደንብ የሰለጠኑ አስተማሪዎች ያስፈልገዋል፡፡ ባንቴ (2017) መምህራን የማንበብ እና የመጻፍ መመሪያን በማጣመር ስልቶችን የሚያስታጥቁ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥቷል፡፡ ስልጠናዎች የተቀናጁ ተግባራትን እና ምዘናዎችን በመንደፍ እና በመተግበር ላይ እንዲሁም በሁለቱም ክሂሎች የተማሪዎችን እድገት የሚደግፉ ውጤታማ ግብረመልሶችን እንዴት መስጠት እንደሚቻል የመምህራን ስልጠና እና ሙያዊ እድገት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ማለት አንዱን ክሂል ከአንዱ ክሂል ጋር አጋጥሞ ወይም አስማምቶ ማቅረብ ነው፡፡ለምሳሌ የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር መናገርና ማንበብ ያስፈልጋል፡፡አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማስተማር ደግሞ በጥሩ ሁኔታ ተቀነባብሮ የተፃፈ ፅሁፍ መኖር አለበት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ክሂል ለማስተማር ሲባል ፤የተለያዩ ክሂሎችን የሚቀርቡበት ሁኔታ ይኖራል፡፡በመሆኑም የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ይህንን የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ማሪው ዓለሙ(2007፡ 112) ሲገልፁ አንብቦ መረዳትን በማስተማር

ሂደት ከማንበብ በፊት፣ በማንበብ ሂደትና ከማንብበ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ ለውጤታማ ትምህርት ያበቃል፡፡ በእያንዳንዱ ደረጃ የሚጠየቁት ጥያቄዎች ተግባርም (ዓላማ) የተለየ ነው፡፡

ከማንበብ በፊት የሚጠየቁት ጥያቄዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የሚነበበውን ፅሑፍ ርዕስ ጉዳይ አስመልክቶ አንባቢዎች የተሟላ ዳራዊ ዕውቀት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩንአስመልክቶ ያላቸውን ዳራዊ ዕውቀት እንዲፈትሹ ያግዛል፡፡ ለተማሪዎች ጽሑፍን የሚያነቡበትን ዓላማ ለመወሰን ይረዳሉ፡ ለምሳሌ፡- ስለዚህ ጉዳይ የምታውቁት ምንድን ነው? ከዚህ በፊት ከምታውቁት በመነሳት ከዚህ ታሪክ ቀጥሎ ምን ይሆናል? ወይም ምን ይመጣል? ብላችሁ ትገምታላችሁ? ወዘተ የመሳሰሉ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ጠቀሜታ አላቸው ይላሉ፡፡

ከላይ ያለው እንደገለጹት ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ለማስተማር ከምንባብ በፊት፤ በማንበብ ጊዜ እና ከማንበብ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚያጎለብት መሆን ተገልጿል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የማንበብ ክሂል ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ያዳብራል፡፡ መጋቢው (2009) እንደሚገልፁት፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲዳብር ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር፣ ስለሌሎች ለማወቅ፣ የረቀቀ አስተሳሰብን ለማጎልበትና ከዓለም ህዝብ መረጃ ለማግኘት ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ በመሆኑም ይህን ጉልህ ፋይዳ ለማረጋገጥም ሆነ አዳዲስ ገጽታዎች ለመመርመር በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን በአንብቦ መረዳትና በአፅምሯዊ ብልሃቶች ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች (ለምሳሌ፣ በጎሰው፣ 2003፤ Anne, 2014; Chanyalew & Abiy, 2015; ዘውዱ፣ 2008) አሉ፡፡

የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎት ውህደት ውጤታማ የሆነ የቋንቋ ትምህርት የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ ይህ ጥናት እነዚህ ክሂሎች በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ እንዴት እንደተጣመሩ ይመረምራል፣ የተማሪዎችን እድገት ምን ያህል በብቃት እንደሚደግፉ ይገመግማል:: የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘት፣ የማስተማር ዘዴዎችን እና የግምገማ ልምዶችን በመተንተን ጥንካሬዎችን እና መሻሻሎችን መለየት ላይ ትኩረት ያደርጋል::

የይዘት ትንተና  የንባብ እና የመፃፍ ችሎታዎች ውህደት በተመለከተ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት የተነደፈው የማንበብና የመጻፍ ሥራዎችን ማንበብና መጻፍን ለማጎልበት ነው:: አለማየሁ (2015) በውጤታማነት ውህደት ምንባቦችን እንደ አብነት በመጠቀም ለአጻጻፍ ስራዎች እና የጽሁፎችን ሂሳዊ ትንተና የሚያበረታቱ ስራዎችን መፍጠርን እንደሚያካትት ገልጿል:: ይህ አካሄድ ተማሪዎች የማንበብ የመረዳት ችሎታቸውን በጽሑፎቻቸው ላይ እንዲተገብሩ ያረጋግጣል:: ለምሳሌ፣ ተማሪዎች የትረካ ፅሑፍ አንብበው ከዛም የፅሁፉን ጭብጦች እና ገፀ ባህሪያቶች መረዳታቸውን የሚያንፀባርቅ ምላሽ ሊፅፉ ይችላሉ::

ባንቴ (2017) በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ሁለቱንም የማንበብ ግንዛቤ እና የፅሁፍ ብቃትን የሚያበረታቱ የተለያዩ ተግባራትን አስፈላጊነት አፅንዖት ይሰጣል:: ይህም ተማሪዎች ፅሁፎችን የሚመረምሩበት እና ያነበቡትን እንዲያንፀባርቁ ወይም እንዲተቹ የሚፈልጓቸውን የፅሁፍ ልምምዶች የሚሳተፉበት ነው:: እንደዚህ አይነት ተግባራት ተማሪዎች ስለ ጽሁፎቹ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ እና ሀሳባቸውን በጽሁፍ በግልፅ የመግለፅ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ይረዷቸዋል::

የባህል እና የቋንቋ አግባብነት በተመለከተ ሥርዓተ ትምህርቱን ከተማሪዎች ልምድ ጋር እንዲገናኝ ለማድረግ የባህል እና የቋንቋ አካላትን ከንባብ እና ከመጻፍ ጋር መቀላቀል ወሳኝ ነው:: ደረጀ ገብሬ (2018) የኢትዮጵያን ባህል እና ታሪክ የሚያንፀባርቁ ፅሁፎችን ማካተት የተማሪዎችን ተሳትፎ እና ግንዛቤ እንደሚያጎለብት ይናገራል:: ማንበብ እና መጻፍ ክሂሎችን ለማዳበር ና የበለጠ ትርጉም ያለው እንዲሆን ለማድረግ  ስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የአካባቢ ስነ-ጽሁፍ እና ታሪካዊ ሰነዶችን በመማሪያ መሳሪዎች ውስጥ  መጠቀም አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ስለአካባቢው ልማዶች ወይም ታሪካዊ ክንውኖች እንዲጽፉ የሚጠይቁ ስራዎች ትምህርታቸውን ከግል እና ባህላዊ አውድ ጋር ለማገናኘት ይረዳሉ::

በተጨማሪም መኮንን (2019) የተቀናጀ የማንበብ ትምህርትን በብቃት በመተግበር ረገድ መምህራን ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ ጠቁመዋል:: መምህራን የማንበብ እና የመጻፍ መልመጃዎች እንዴት ማዋሃድ እና የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ለማንፀባረቅ የትምህርት

መሳሪያዎች ማላመድ እንዲችሉ ሙያዊ ማዳበር ዕድሎች አስፈላጊ ናቸው። በቂ ስልጠና ከሌለ መምህራን አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎቶች ውጤታማና አግባብ ባለው መንገድ ለማዋሃድ (ለማቀናጀት) ሊያስቸግራቸው ይችላል።

ግምገማ እና ግብረመልስ በተመለከተ ውጤታማ የምዘና ልምዶች የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን ውህደት(ቅንጅት) ለመገምገም ወሳኝ ናቸው። ተክሌ (2020) ምዘናዎች ሁለቱንም ክሂሎች በአንድ ጊዜ ለመለካት በሚያስችል መልኩ መቀረጽ እንዳለባቸው ይጠቁማል። ይህም የተማሪን የብቃት ደረጃ የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ፣ በምንባቦች ላይ ተመስርተው እንደ ድርሰቶች መፃፍ ያሉ ተግባራትን ያካተቱ ግምገማዎች ተማሪዎች የማንበብ ግንዛቤያቸውን በፅሁፍ ላይ ምን ያህል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ይገመግማሉ። ለተማሪዎች የሚሰጠው የአስተያየት ጥራት ሌላው የተቀናጀ ትምህርት አስፈላጊ ገጽታ ነው። የግብረመልስ ዘዴዎች ተማሪዎች ሁለቱንም የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት አለባቸው። ይሁን እንጂ ግብረመልስ በአሁኑ ጊዜ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና በተማሪ አፈጻጸም ላይ ያለውን ተጽእኖ በመረዳት የምርምር ክፍተቶች አሉ። ግብረመልስ ወደ ትምህርት እንዴት እንደሚዋሃድ እና የተማሪን እድገት በብቃት ለመደገፍ እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ላይ ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ።

የምርምር ክፍተቶች  በውጤታማነት ላይ ተጨባጭ መረጃ በተመለከተ  የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎትን በማቀናጀት ውጤታማነት ላይ ተጨባጭ መረጃ እጥረት አለ። ይህ አካሄድ የተማሪን የትምህርት ውጤት ምን ያህል እንደሚደግፍ ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ በተቀናጀ የንባብ እና የመጻፍ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች የተለየ ትምህርት ከሚቀበሉት ጋር ሲነፃፀሩ በሁለቱም ዘርፎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳላቸው ጥናቶች ሊመረምሩ ይችላሉ።

የአስተማሪ እይታዎች በተመለከተ  ሌላው ክፍተት የመምህራንን የንባብ እና የመጻፍ ክህሎት ውህደትን በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት መረዳት ነው። ጥናቱ መምህራን የተቀናጀ ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል የሰለጠኑ እንደሆኑ እና የሚያጋጥሟቸውን

ፈተናዎች መመርመር ይችላል። መምህራን ውጤታማ የተቀናጀ የማንበብና የማንበብ ትምህርት ለማዳረስ ሙያዊ ልማት እና ድጋፍ ሥርዓቶች መገምገም አለባቸው።

ባህላዊ እና አውዳዊ ምክንያቶች በተመለከተ ሥርዓተ ትምህርቱ የተለያዩ የባህልና የቋንቋ ዳራዎችን በምን መልኩ እንደሚያስተናግድ የተወሰነ ጥናት አለ። ሥርዓተ ትምህርቱ የተማሪዎችን ባህላዊ አውዶች በሚገባ የሚያንፀባርቅ መሆኑን እና የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን ለመገምገም ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ። ይህ የአካባቢ ፅሁፎች እና ባህላዊ አካላት ምን ያህል በንባብ እና በመፃፍ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደተካተቱ መመርመርን ያካትታል።

የግምገማ ልምዶች በተመለከተ የተቀናጀ የማንበብ ክህሎትን ውጤታማነት በመረዳት ረገድም ክፍተቶች አሉ። ጥናቶች ሁለቱንም የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን ለመገምገም እና አጠቃላይ የተማሪን ችሎታዎች ለመለካት እንዴት እንደተዘጋጁ ምርምር ሊያተኩር ይችላል። በተጨማሪም፣ የተማሪ መሻሻልን ለመደገፍ ግብረመልስ እንዴት እንደሚቀርብ እና ጥቅም ላይ እንደሚውል መመርመሩ የግምገማ ልምዶችን ስለማሳደግ ግንዛቤዎችን ይሰጣል።

የተማሪ ተሳትፎ እና ውጤቶች ተመለከተ የተቀናጀ የማንበብ እና የመጻፍ ተግባራት የተማሪ ተሳትፎን እና ተነሳሽነትን እንዴት እንደሚነኩ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። የረዥም ጊዜ ጥናቶች እነዚህ ተግባራት ለተማሪዎች አጠቃላይ የማንበብ እድገት እና የአካዳሚክ አፈጻጸም ምን ያህል አስተዋፅዖ እንዳበረከቱ ሊዳስሱ ይችላሉ። የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ለማሳደግ ከመንገት በመነጨ ብዙ ተመራማሪዎች (Chanyalew & Abiy, 2015; እንድሪስ፣ 2009፤ ሙሉገበያ፣ 2009፤ Teshale & Yemanebrhan, 2015; ዘውዱ፣ 2008፤) የተለያዩ የመማርና የማስተማር ብልሐቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት መርምረዋል። ዘውዱ (2008) በኢትዮጵያ የሚሰጠው የማንበብ ትምህርት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና ተነሳሽነት የሚያሳድግና የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሂደትን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ይገልፃሉ። በጎሰው (2003) በአዲስ አበባ ከተማ የነባርና የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ላይ ባደረጉት ጥናት የነባርም ሆነ

የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ደካማና መሻሻል የሚገባው እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ Teshale & yemanebrhan (2015) በቦንጋ መምህራን የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች የንባብ ልምምድ ፍተሻ አድርገው አብዛኞቹ ተማሪዎች ከቃል ትርጉም ደረጃ ንባብ ውጭ ብልሃትን ዘዴን መሰረት ያደረገ የንባብ ሂደት በመተግበር እንዳልተጠቀሙ ያሳያሉ፡፡ Chanyalew & Abiy (2015) የመምህሩ ድጋፍ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና ፈትሸው ድጋፍ የተሰጠው የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ተማሪዎችን አንብቦ ለመረዳት ውጤታማ በመሆኑ፣ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ስለድጋፍ ሰጪ የማስተማሪያና የመማሪያ ስልጠና በስፋት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ የሙሉገበያ (2009) ጥናት የፅሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ፈትሿል፡፡ ውጤቱም የፅሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ያሳያል፡፡ እንድሪስ (2005) በደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የንባብ ፍላጎት፣ የንባብ ልምድ፣ የጥናት ክሂሎችና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ መርምረው የማንበብ ብልሃቶችን በአግባቡ ተገንዝበው በተለያዩ መንገዶች ማንበብን መከወን አለመቻላቸው የማንበብ ልምድ እንቅፋት መሆኑን አሳይተዋል፡፡

በLau & Chan (2003) ጥናት የማንበብ ብልሃት ዕውቀትና የመጠቀም ችሎታ ከአንብቦ መረዳትና ከተነሳሽነት ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸውና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ እንደሆኑም ተገልጿል፡፡ የYussof, et al (2012) ጥናት ደግሞ አዕምሯዊና ንድፋዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ ከግንባታውያን አስተያየት አንጻር የተሰራው ፍጥነት መሰል ጥናት አዕምሯዊና ንድፋዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንደሚያሳድግ አሳይቷል፡፡ የAnne (2014) ጥናት አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃት መጠቀም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ ያለው ሚና እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች (EFL) የተሰራው ጥናት፣ ከአዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ የትኛው አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃት ውጤታማ መሆኑን ለማሳየት ነበር፡፡ ጥናቱም አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች በጥምረት ደጋግሞ መስራት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደካማ ለሆኑ

ተማሪዎች ይበልጥ ውጤታማ እንደሆነ አሳይቷል። በመሆኑም አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችንና አገልግሎታቸውን መማር እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የSuyitno (2017) እና Shew (2017) ጥናቶች አዕምሯዊ ብልሃቶችን መጠቀም ለአንብቦ መረዳት ችሎታና ለውጤት ያለው አስተዋፅኦ በኢንዶኖዥያ ቋንቋ በተፃፉ ምንባቦች ላይ መርምሯል። ውጤቱም ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና ውጤት የብልሃቶች አመራረጥ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ይጠቁማል። ማለትም፣ ለራሳቸው የሚሆነውን (የማንበብ ልምድ ያላቸውና የሌላቸው ተማሪዎች መርጠው መጠቀም አለባቸው)። ምክንያቱም አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው።

በተለይ ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው የሀገር ውስጥ ጥናቶች (እንድሪስ፣ 2009፤ የዘውዱ፣ 2008) ማንበብን በመማር የተለያዩ ብልሐቶች በአንብቦ መረዳትና በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያላቸውን ፋይዳ በመፈተሽ ላይ አተኩረዋል። የእንድሪስ (2009) የቴክስት ውቅር ብልሃቶች ማንበብን መማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ውጤት፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ የማንበብ ግለ ብቃት እምነትና ትኩረት እንደሚያሻሽል በጥናታቸው አመላክተዋል። የዘውዱ (2008) ጥናት፣ ተማሪዎችን የሚና ለዋጭ ዘዴ አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውንና የማንበብ ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ አስተዋፅኦ እንዳለው በግልፅ አሳይቷል።

ነገርግን ከላይ ያየናቸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀደምት ጥናቶች ለአንብቦ መረዳት አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሂደትን፣ ብልሃትን መሰረት ያላደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በመሆኑም ከ2015 ዓ.ም በፊት ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ተዘጋጅቶ ሲያገለግል የነበረውን መጽሐፍ አጥኝው ተመልክቷል። አንብቦ በመረዳት እና የጽህፈት ክሂልን አዋህዶ ማቅረብ በተለያዩ ተመራማሪዎች ጥናቶች ቢኖሩም ከላይ የተዘረዘሩትን የምርምር ክፍተቶች ለመፈተሽ በ2015 ዓ.ም በአዲስ መልክ የተዘጋጀው ወይም ስራ ላይ የዋለው አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ መቅረብና አለመቅረቡን ለመዳሰስ አጥኝው ተነሳስቷል።

በመሆኑም ከዚህ በታች የተገለጹትን ዋና ሀሳቦች ጫፍ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚመረምር ይሆናል፡፡

1. መጽሐፉ የመፃፍ ክሂል እና አንብቦ በመረዳት ክሂልን አዋህዶ ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቅርቧል?
2. የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማርየቀረቡትን ( የተዘጋጁትን) ምንባቦች ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋ ግልፅነት አላቸው?
3. በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ትዕዛዝ ግልፅነት ምን ይመስላል ?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በ2015 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍል ለመማሪያ የተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ችሎታ ቅንጅታዊ አቀራረብ የሚመለከት ነው፡፡ ጥናቱን ለማሳካት ዝርዝር አላማዎች የሚቃኝ ይሆናል

ሀ. በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል እና የአንብቦ በመረዳት ክሂልን አዋህዶ ይዘቶችንና መልመጃዎችን መቅረብና አለመቅረባቸውን መመርመር እና መተንተን፥

ለ. የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ምንባቦች የቋንቋ ግልፅነት ማየት፥

ሐ. በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ትዕዛዝ ግልፅነት መመርመር፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ የምርምር ስራ በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አዋህዶ ማቅረብና አለመቅረቡን ማየት ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የሚከተሉትን ፋይዳዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- →አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረባቸውን ስለሚቃኝ ለመምህራን አቅጣጫ ያሳያል፡፡
- →በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ትዕዛዝ ግልፅነትን ስለሚመረምር ለተማሪዎችም ጠቀሜታ አለው፡፡
- →በዚህ ርዕስ ላይ ለወደፊት ምርምር ለሚያደርጉ አጥኚዎች እንደ መነሻ ይሆናል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የተካሄደው በቤኒሻንጉል ክልል በ2015 ዓ.ም የታተመው አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ሲሆን ርዕሱ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ የታተመው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ የተማሪው መፅሀፍ ላይ ያተኮረ ነው ፡፡ይህ ጥናት መፅሀፉ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂልን አቀናጅቶ ማቅረቡን የሚገመግም ነው ፡፡በመሆኑም አጥኝው የተጠቀመው የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች የሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ስለዚህ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሟላ መረጃ ሊገኝ አይችልም ፡፡ፍፁም ያለቀለት ነው ማለት አይቻልም ፡፡የመፅሀፉ አዘጋጆች ከቦታ ርቀት አኳያ አጥኝው ለመረጃ ምንጭነት አላካተታቸውም ፡፡ስለዚህ ጥንታዊ ውስንነት አለበት፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ብያኔ

1. **አንብቦ መረዳት ፡-** በዚህ ጥንታዊ ፅሁፍ አንብቦ መረዳት የሚለው ቃል የሚገልፀው ተማሪ ዎች ለማንበብ ክሂል ከቀረበላቸው ፅሁፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ፅሁፉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት መለየት ነው ፡፡ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ከራሳቸው የቀደመ ዕውቀት ጋር በማያያዝ ትርጉም ያለው ሀሳብ የሚሰጡበት አእምሯዊ ሂደት ነው ፡፡

2. **የመፃፍ ክሂል ፡-**የፅህፈት ክሂል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ እና እየተሻሻለ የሚመጣ ክሂል ነው ፡፡ አንድ ፀሀፊ ለመፃፍ ሲነሳ በርካታ ነገሮችን ያገናዝባል ፡፡ ስለ ምን እንደሚፅፍ ፣ለምን እንደሚፅፍ ፣ለማን እንደሚፅፍ ፣የቃላት አመራረጥ ግንዛቤ የሚጠይቅ ክሂል ነው ፡፡የመፃፍ ክሂል በባህሪው ክሂለ ብዙ ነው ፡፡የሀሳብ አደረጃጀት ፣የአንቀፅ አመሰራረት ፣የዓረፍተ ነገር አወቃቀር የቃላት አመራረጥ ፣የሚጠይቅ ክሂል ነው ፡፡የመፃፍ ክሂል እየፃፉ መማርን የሚጠይቅ ክሂል ነው ፡፡

3. **ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ፡-**የቋንቋ ክሂሎች የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም ፣አንዱን ክሂል ብቻ አስተምራለሁ ብሎ ማሰብ አይቻልም ፡፡የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር ንግግርና ማንበብ መኖር አለበት ፡፡የማንበብ ክሂል ለማስተማር የተፃፈ ፅሁፍ መኖር አለበት ፡፡ስለዚህ

አንዱን ክሂል ለማስተማር ስንነሳ ሌላኛውን ክሂል ጨምረን የምናስተምር ከሆነ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ይባላል ማለት ነው ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት:-ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ሀሳቦችን እና የተመራማሪዎችን ስራ የሚቃኝበት ክፍል ሲሆን በዚህ ምዕራፍ የሚካተቱት የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ምንነት፣ የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ባህሪያት፣ የመማሪያ መፅህፍት ይዘት አዘገጃጀት፣ የቋንቋ ክሂሎች አዋህዶ ማቅረብ፣ የማንበብ ምንነት፣ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ፣ ድህረ ንባብ ተግባራት፣ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ፣ የመፃፍ ክሂል ምንነት፣የመፃፍ ችሎታን ለማዳበር እና የቀደምት ስራዎች ቅኝት የሚታይበት ምዕራፍ ነው፡፡

ያለው እንዳወቅ (2006፤ 68) ይህንን ሀሳብ ሲገልጹ *ምርምር ለማድረግ ስንነሳም በመጀመሪያ ያለውን ዕውቀት ተመርኩዞን ነው፡፡ ምርምርን ለማካሄድ ያለውን ዕውቀት በመጠቀም የተነሱበትን ርዕሰ ጉዳይ ማብራራት፣ምርምር በሚካሄድበት ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ምን እንደተደረገ፣የተገኘውን ውጤት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን እንደሆኑ ስራ ውስጥ ማመልከት በምርምር ቋንቋ የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ ይባላል፡፡* ያለው እንደገለጹት የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ ማለት አንድ ተመራማሪ ለሚያጠናው ጥናት መንገድ የሚያሳይ ወይም ዕውቀት የሚሰጥ ነው፡፡ ተመራማሪው በተለያዩ ምሁራን የተሰሩ ስራዎችን በማንበብ ባገኘው ዕውቀት መሰረት የራሱን ጥናት የሚያጠናበት ነው፡፡

### 2.1 የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች

የቋንቋ ማስተማሪያ የምንላቸው መርሃ ትምህርት፣ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ፣የመምህሩ መምሪያ ሲሆን፣እነዚህ መሳሪያዎች ቋንቋን ለማስተማር ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

#### 2.1.1 መርሃ ትምህርት

መርሃ ትምህርት በትምህርት መስክ በየትምርህት ደረጃው የሚዘጋጅ የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡ በየትምህርት ዓይነት የትምርህቱ ይዘት፣ የመምህሩ ተግባር፣ የተማሪው ተግባር፣የማስተማሪያ ስነ ዘዴ፣ የትምህርቱ መገምገሚያ የሚቀርብበት የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡

Ur (2009) ስለመርሃ ትምህርት ሲገልፁ በአንድ የትምርህት ተቋም በየክፍል ደረጃው የሚቀርብ ዝግጂት ሆኖ በየትምህርት ዓይነቱ የተቀነባበሩ ይዘቶችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የመገምገሚያ መሳሪያዎችን የሚያመላክት መግለጫና ለመማር ማስተማሩ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪው ከአካባቢው የሚገኘውን የህይወት ልምድና ዕውቀት በመጠቀም የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚሰራበት የትምህርት ዕቅድ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ስለ መርሃ ትምህርት Ur (2009) እንደገለጹት መርሃ ትምህርት ማስተማሩ የተዘጋጀ የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡ ይህ ሲባል ትምርህቱ የሚሰጥበት ዕለት፣ የትምርህቱ ይዘት፣ የተማሪውና የመምህሩ ተግባር፣የትምርህቱ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ፣ ትምርህቱ የሚሰጥበት ጊዜ፣የትምርህቱ ውጤት አጠቃሉ የያዘ የትምህርት ዝግጅት ነው፡፡

## 2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት

መፃህፍት በዓይነታቸው በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሀይማኖት መፃህፍት፣የልቦለድ መፃህፍት፣የተማሪው መማሪያ መፃህፍት የመሳሰሉት ሲሆን፣ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተማሪዎችን ታሳቢነት በማድረግ የሚዘጋጅና እውነታን ያዘለ፣ በእኩልነት የሚያገለግል የመማሪያ መሳሪያ ነው፡፡

*ፀጋየ ጎረጋይ 1977)* Good የሰጠውን ብያኔ ዋቢ በማድረግ ስለመማሪያ መፃህፍት ምንነት እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> *የመማሪያ መፃህፍ በሥርዓት ተቀናጅቶ አንድን የትምህርት ዓይነት በመያዝ ለአንድ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ ለማስተማሪያነት ተዘጋጅቶ የመማር ማስተማር ሂደትን በመምራት አንድ ምዕራፍ የሚደርስና ለተተኳሪው ትምህርት ጥናት እንደ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል መሳሪያ ነው (1977፤ 605)*

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በሥርዓት በመዘጋጀት ለተወሰነ የክፍል ደረጃ ለመማር ማስተማር ተዘጋጅቶ ሂደቱን የሚመራ ነው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተማሪዎችን የኑሮ ደረጃ፤ ዕድሜ፤ የክፍል ደረጃ ታሳቢ በማድረግ የሚዘጋጅ የትምህርት መሳሪያ ነው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሀቀኝነት ያለው፣ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላው የክፍል ደረጃ የሀሳብ ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት፡፡

### 2.1.3 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህሪያት

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከሌሎች ዓይነቶች የሚለይባቸው የራሳቸው ባህሪያት ይኖራቸዋል፡፡ የመማሪያ መፃህፍት የሚፃፍበት ቋንቋ መደበኛ የሆነ ወይም ከአካባቢያዊ አነጋገር ( ዘዩ) የለለበት ማንኛውም ማህበረሰብ ቋንቋውን የሚረዳ መሆን አለበት

እመቤት በጥናታዊ ምርምር ስለ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህሪያት ተስፋየ (1981) ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ገልፃለች፡፡

> *ለተወሰኑ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እንድሆኑ ታስበውና ይሆናሉ ተብለው የሚዘጋጅ መፃህፍት በሚዘጋጅበት ወቅት እውነተኛነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ተግባራዊነት፣ ተገቢነት የሚሉትን ባህሪያት ማሟላት አለበት*

**እውነተኝነት፡-** ለትምህርት የቀረበው የትምህርት አካል እውነት የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚለው መሆን አለመሆኑን የሚዳኝበት ነው፡፡ ተማሪው እንዲማር፣ እንዲለማመደው የሚረዳው የቋንቋ አካል ቋንቋውን ይበልጥ የሚያሳውቅ በቋንቋው በተማሪው ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድር መሆን አለበት፡፡

**ግልፀኝነት፡-** የማስተማሪያ መሳሪያዎች የያዟቸው የትምህርት ጉዳዮች መምህሩ እንዲያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልፅ መስፈር አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው፡፡

**ተለጣጣቂነት፡-** በአንድ መጽሐፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከል የሆነ ለተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መጽሐፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪው ቀጥሎ የሚደርስበትን ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን የሚደግም ከሆነ ግን እድገት ወይም አዲስነት የለበትምና መሰላቸት ይከተላል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የመማሪያ መጽሐፍት ባህሪያት መጽሐፍ የያዘው ሀሳብ ግልፅ የሆነና ተማሪዎችን ግራ የማያጋባ መሆን እንዳለበት፣በተማሪዎች ሊተገበር የሚችል፣ሀሳቡ የማያጠራጥር፣ እውነተኛ የሆነ የሀሳብ መደጋገም የሌለበት እንደሆነ እና ከአንዱ ወደ ሌላ ክፍል ሲሸጋገር የሀሳብ ተያያዥነት መኖር አለበት፡፡

### 2.1.4 የመማሪያ መጽሐፍት ይዘትና አዘገጃጀት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ሲዘጋጅ ተማሪውን ያስተዋለ መሆን አለበት፡፡ የኀውም የተማሪው ዕድሜ ደረጃ፣ የተማሪው ፆታ፣ ባህልና ወግን የቃኘ፣ ተማሪው ስለቋንቋ ያለው አመለካከት በማየት የሚዘጋጅ የመማሪያ መጽሐፍት ነው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ይዘት በሚዘጋጅበት ወቅት የተማሪው ክህሎት፣ የተማሪው አስተሳሰብ ተማሪውን የሚያጎለብትና የሚያበለጽግ በሚሆን መልኩ የመማሪያ መጽሐፍት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

የመማሪያ መጽሐፍት ይዘትና አዘገጃጀት በተመለከተ ዶ/ር ፀጋየ ለPGDT ማስተማሪያነት ባዘጋጁት ሞጁል ሙርሲ (1991) እና ዊሊያምስ (1995) ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> *የመማሪያ መጽሐፍት በዝግጅት ወቅት ትኩረት የሚሰጣቸው ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም “ ምን ” እና “ እንዴት ” የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ጠያቂ ቃላት የቋንቋውን ትምህርት የሰነ ልሳንና የስነ ልቦና የስነ ትምህርት ይዘት ያሟላ መሆን አለበት ይላሉ፡፡*

በምሁራን እንደገለፁት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት በሚዘጋጅበት ወቅት በምን ዓይነት ሁኔታ መዘጋጀት እንዳለበት እና ምን ምን ነገሮች መካተት እንዳለበት ታሳቢ የሚደረግበት ነው፡፡

### 2.1.5 የቋንቋ ክሂሎች አዋህዶ ማቅረብ

የቋንቋ ክሂሎች የምንላቸው ማዳመጥ፣መናገር፣ መፃፍ እና ማንበብ ሲሆኑ እነዚህ ክሂሎች የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም፣አንዱን ክሂል ብቻ አስተምራለሁ ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር ንግግርና ማንበብ መኖር አለበት፡፡ የማንበብ ክሂል ለማስተማር የተፃፈ ጽሑፍ መኖር አለበት፡፡ ስለዚህ አንዱን ብቻ ነጥሎ ማስተማር የማይሆን ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

ማሪው (2007፤ 139- 140) የቋንቋ ክሂሎች አዋህዶ ማቅረብ ሲገልፁ

> *ክሂሎች የተለያዩ ሲሆኑ ለትምህርት ሲቀርቡ ተነጥለው /ራሳቸውን ችለው ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ አንድ ቀን ተማሪዎች የማንበብ ማንበብ ላይ አተኩረው ሰርተው ከሆነ በሚቀጥለው በመናገር ላይ ብቻ፣በሌላም ቀን እንዲሁ በሌላው ክሂል ላይ ብቻ እያሉ ማሰብ ይቻላል፡፡*

*ይህ መነሻ ሀሳብ ግን በሁለት ምክንያቶች ውድቅ ይሆናል፡፡ አንደኛ ነገር አንድ ክሂል ከሌላ ክሂል ብቻውን አይከወንም፣ሊከወንም አይችልም፡፡ በውይይት ወይም በምልልስ ለምሳሌ ማዳመጥ ካልተቻለ/ ያውም በሚገባ/ መናገር አይቻልም፡፡ ሰዎች ባንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሲሰሩ በተለያየ ምክንያቶች የተለያዩ ክሂሎችን ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የትምህርት ገለፃ የሚያዳምጥ ተማሪ ማስታወሻ ይጽፋል፣ ከዚያም ስለገለጻው ሪፖርት ሊጽፍ ይችላል፡፡ ያው ተማሪ ገለጻውን አስመልክቶ ለጓደኛው በቃል ወይም በጽሑፍ ሊገልፅ ይችላል፡፡*

ማረው እንድገለፁት ክሂልን በምናስተምርበት ጊዜ ነጣጥሎ ማስተማር ወይም አንድን ክሂል ብቻ ማስተማር የማይቻል መሆኑ፣ ለምሳሌ፡- የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር ማንበብ ወይም መናገር ያስፈልጋል፡፡ ጽህፈትን ለማስተማር መናገር፣ማንበብና ማዳመጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አንድን ክሂል ስናስተምር ሌለኛው ክሂል መነካካታችን አይቀሬ ነው፡፡

## 2.2 የማንበብ ምንነት

የማንበብ ምንነት  በተለያየ ሁኔታ በጽሑፍ ተቀርፀው የሚገኙትን ጽሑፎች ስሜታችንን ሰጥተን ማንበብ ማለት ነው፡፡ ማንበብ የዕውቀት አድማሳችንን የሚያሰፋ፤ ለአእምሮ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያለው፣ ከተለያዩ ጎጂ ነገሮች በማንበብ የምንድንበት ነው፡፡

የማንበብ ምንነት ደረጃ ገብሬ ( 2013፤ 14- 21)

*የተለያዩ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች የማንበብን ምንነት በሚመለከት በርካታ ብያኔዎች ሲሰጡ ኖረዋል፣እየሰጡም ይገኛሉ፡፡ እንደ ተፈላጊነቱ መጠን ብያኔ የመስጠቱ ጉዳዩ ወደ ፊት የሚቀጥል መሆኑ ይገመታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ማንበብ ማለት ከፊደሎች ትውውቅ እና ንባብ በላይ የሚገኘውን የመረዳትን ሀሳብ የሚጠቁም ነው፡፡ ስለማንበብ ምንነት ጨመቅ የተደረገ ብያኔ ከመስጠጥ በተለየ ሁኔታ በዝርዝር መከሰታቸው በሚከተሉት ነጥቦች ማየት ይቻላል፡፡*

ማንበብ አንድን ፅሑፍ ተጠቅሞ በአእምሮ ውስጥ ፍቺ የመፍጠር ተግባር ነው፡፡ ማንበብ በዘላቂነት እያደገ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ ማንበብ ግልፅና ስውር መረጃዎችን ማገናኛ ተግባር ነው፡፡ ማንበብ ሆሄያትንና ቃላትን መቁጠር ሳይሆን አንድን ሀሳብ ከሌላ ጋር የማገናኘት/ ማያያዝ ተግባር ነው፡፡

እንደ ምሁራን ገለፃ ማንበብ ማለት የቀረበልንን ፅሑፍ በጥሞና በማንበብ ከራሳችን የቀደመ ዕውቀት ጋር በማያያዝ ለፅሑፍ ብያኔ መስጠት ነው፡፡ ማንበብ ከዕለት ወደ ዕለት እየዳበረ እና እየበለፀገ የሚሄድ ነው፡፡ ማንበብ አዳዲስ መረጃዎችን የምናገኝበት ነው፡፡

## 2.3 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ

የአንብቦ መረዳት ትምህርት ለማስተማር በቅደም ተከተል የምናከናውናቸው ስራዎች አሉ፡፡ ወደ ምንባብ ከመግባታችን በፊት ስለምንባቡ ያለን የቀደመ ዕውቀት መግለፅ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በንባብ ወቅት ለቃላት ፍች መስጠት የደራሲውን ሀሳብ የምንረዳበት ወይም ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ የምንረዳበት የንባብ ጊዜ ተግባራት ሲሆን በመጨረሻ ያነበብነውን ምንባብ ፅንስ ሀሳቡን መረዳታችንን የምንፈትሽበት ሁኔታ ድህረ ንባብ ተግባር ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ምሁራን እንደሚከተለው በሰፊው ገልፀዋል፡፡

በድሉ (2007) ቅንጫቢን በመጠቀም አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማስተማር በአብዛሃኛው የሚያገለግሉ ሦሥት ዘዴዎች አሉ፡- እያንዳንዱ ተማሪ በራሱ ፍጥነት በዝምታ የሚነብበት ዘዴ፤ መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያነብ ተማሪዎች በዝምታ እያነበቡ የሚከተሉበት ዘዴ እና ተማሪዎች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚያነቡበት ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎች ለንባብ የሚነሳሱ ቅድመ ንባብ ተግባራትን መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.3.1 ቅድመ ንባብ ተግባራት

ቅድመ ንባብ ተግባራት ማለት ወደ ዋናው ንባብ ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመፈተሽ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው መልስ የሚሰጡበት ነው፡፡

ምንባቡ ስለምን ጉዳይ የሚያትት እንደሆነ ግምታቸውን የሚያስቀምጡበት ነው፡፡

> *ይህንን ሀሳብ በድሉ (2007፤ 43) እንደሚከተለው ያጠናክሩታል፡፡ቅድመ ንባብ አስፈላጊነቱ አጉልቶ ለማሳየት ስለንባብ አጠቃላይ ነጥቦችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ በእውነተኛው ህይወት ( ከመማሪያ ክፍል ውጭ) የምናነበው ለማንበብ ብቻ ብለን አይደለም፡፡ የምናነበው ማንበብ ስለምንፈልግ ነው፡፡ ፍላጎት የሚመነጨው ደግሞ ከምክንያት ነው፡፡ ከምናነበው ቅንጫቢ ውስጥ የምንፈልገው አዲስ ነገር ግልጽ የምናደርገው ወይም የምናረጋግጠው ሀሳብ ሲኖር ነው የምናነበው፡፡ አብዘሃኛውን ጊዜ ንባብ የምንጀምረው በባዶ ጭንቅላት አይደለም፡፡ ስለምናነበው ጉዳይ የተወሰነ*

*ነገር፤ ሃሳብ ወይም ጥያቄዎች ይኖሩናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የምናነበው ሀሳብ በተመለከተ መላምቶችን ይዘን ማንበብ እንጀምራለን።*

ከዚህ በላይ በድሉ እንደገለጹት ቅድመ ንባብ ተግባራት ወደ ዋናው ንባብ ከመግባታችን በፊት የራሳችንን የቀደመ ዕውቀት የምናቀርብበት ተግባር ነው። በቅድመ ንባብ ተግባራት የሚቀጥለው ንባብ ስለምን ጉዳይ ሊያነሳ እንደሚችል የምንተነብይበት ነው።

## 2.3.2 የንባብ ተግባራት

ንባብ ተግባራት ማለት ሃሳባችንን ሰብሰብ አድርገን ንባቡ የሚያስተላልፈውን መልዕክት የምንረዳበት ነው። ከዚህ ባሻገር በንባብ ጊዜ ለሚያጋጥሙን አዳዲስ ቃላት በንባቡ አውድ መሠረት ፍቺ እየሰጠን የደራሲውን ሀሳብ የምንገነዘብበት ነው።

በድሉ (2007፤ 50, 51) ሲገልጹ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ማስገባት አለባቸው (block, 1993) ቀደም ብለው የገመቱትን ሃሳብ ከቅንጫቢው ከሚገኙት ሃሳብ አንፃር ማሻሻል በየአንቀፁ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ የሆነው ሃሳብ የትኛው እንደሆነ መለየት፣ ግራ የገባቸውን እያጣሩ መሄድ፣በየመሃሉ ቆም እያሉ ከሚያነቡት ውስጥ የሚያገኙትን መረጃዎች ተጠይቃዊነት መመርመር፣ ከንባባቸው የሚያገኙትን መረጃ በመጠቀም ምስል በህሌናቸው መቅረፅ፣ ማጠቃለያ ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ በትክክል ያልተረዱትን ሃሳብ ካለ ወደ ኋላ ተመልሰው ዝርዝር ሀሳቦችን መመርመር።

ከዚህ በላይ በድሉ እንደገለጹት በንባብ ተግባራት ወቅት አንባቢው ዋና ዋና ሀሳቦችን መለየትና ግልፅ ያልሆኑ ሃሳቦችን ዳግም ከቀደመ እውቀቱ ጋር በማያያዝ ለመረዳት መሞከር እና በምንባቡ አውድ መልዕክቱን መረዳት አለበት።

## 2.3.3 ድህረ ንባብ ተግባራት

ድህረ ንባብ ተግባራት ማለት አንባቢው የቀረበለትን ፅሁፍ ምን ያህል እንደተረዳው የሚገመግምበት ተግባር ነው። አንድ አንባቢ የምንባቡን ሀሳብ መረዳቱን ለመፈተሽ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎች ይዘጋጃሉ። የቀረቡትን ጥያቄዎች በትክክል ከመለሰ የምንባቡን መልዕክት ተረድቶታል ማለት ነው።

በድሉ( 2007፣45-51) ድህረ ንባብ ተግባራትን ሲገልፁ፡-የተለመደው የድህረ ንባብ ተግባር የተነበበውን ቅንጫቢ መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን መመለስ ነው። እንዚህ ጥያቄዎች የቃላትን ፍች ከመጠየቅ ጀምሮ አጠቃላይ የቅንጫቢውን ፍሬ ሃሳብና የፅሃፊውን

አመለካከት እስከ መጠየቅ ይደርሳል፡፡ ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች የትምህርቱን አላማ ከተከተሉና በትክክል ( ከአጠያየቅ ብልሀቶች አንፃር) ከቀረቡ አስፈላጊነታቸው አጠያያቂ አይሆንም፡፡

ከላይ በድሉ እንደገለፁት በመጨረሻ ቅንጫቢዎችን አንብበው ምን ያህል ሃሳብን እንደተረዱት ለመፈተሽ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጽሀፊውን አመለካከት እስከ መጠየቅ የሚደረስበት ተግባር መሆኑን ተገልጧል፡፡

## 2.4 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ ስንል በትክክል ምንባቡን አንብበን በተረዳነው መልኩ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲቀርቡ በተለያየ አይነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በምርጫ፣ እውነት ወይም ሀሰት፣ በምርጫና አዛምድ በመሳሰሉት ይቀርባሉ፡፡ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ምንባቡን ያላነበበ ሰው የሚመልሰው ከሆነ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ቀርቧል ለማለት አያስችልም፡፡

ይህንን ሀሳብ ሙሁራን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡

፡ ታደሰ (2007) ግሬሴት1981፣ ዴቪስ 1995 ዋቢ በማድረግ PGDT በማስተማሪያነት ባዘጋጁት ሞጁል ሲገልፁ፡-

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በፅሁፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ አቀራረባቸው በክፍት አጠያየቅ፣ በምርጫ፣ በእውነት ወይም ሀሰት በሉና በሌሎች መንገዶች ሊቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄዎች የሚቀርቡበት መንገድ የተለያየ ሊሆን ቢችልም እንዚህ ጥያቄዎች ግን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት ሊያደርጉ ይችልሉ፡፡

- ጥያቄዎች በአንድ በተወሰነ የተወሰነ የምንባብ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆን ሁሉንም ምንባብ (ፅሁፍ) በሚያስቡበት ምንገድ የሚዘጋጁበት ለመመርመር ይገባል፡፡
- የጥያቄዎቹ ቁጥር ሳይበዛና ሳያንስ በቂ መሆን እየተረጋገጠ መዘጋጀት አለበት፡፡
- ጥያቄዎች በአቀራረባቸው የተለያዩ የማቅረቢያ መንገዶችን ተከትለው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡

ከላይ በሙህራን እንደተገለፀው ለአንብቦ መረዳት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች የተወሰን የምንባቡን ክፍል የያዙ መሆን የለባቸውም አጠቃላይ የቀረበውን ምንባብ ያካተተ መሆን አለበት፡፡ የሚቀርቡት ጥያቄዎች የበዛ መሆን እንደሌለባቸው፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንባቡ

ከተዘጋጀበት ቋንቋ የጠነከረ መሆን ተገቢነት እንደሌለው፣ ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት መልሶች ለተማሪው ደረጃ የሚመጥን መሆን እንዳለበት እና ጥያቄዎቹ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተዋህደው የሚቀርቡበት ዘዴ መፈላለግ አስፈላጊ እንደሆነ አስረድቷል፡፡

## 2.5 የመፃፍ ክሂል ምንነት

የፅህፈት ክሂል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረና እየተሻሻለ የሚመጣ ክሂል ነው፡፡ ለመጀመሪ ጊዜ ትምህርት የሚባለውን ነገር ስንጀምር እስክርቢቶና ወረቀትን ለማገናኘት እና ፊደላትን ለመቅረፅ ዳገታችን ነበር፡፡ የፊደላትን ቅርፅ በማወላገድ ለአንባቢ በሚያስቸግር ሁኔታ የምንፅፍበት ጊዜ ነበር፡፡ ነገር ግን በተከታታይ የመፃፍ ክሂላችን እየዳበረ ሲመጣ እስክርቢቶ አስተካክለን በመያዝ ፊደላትን በትክክል ቀርፀን ወረቀት ላይ እናሳርፋለን፡፡

የፅህፈት ክሂል ከዚህ በዘለለ አንድ ፀሃፊ ለመፃፍ ሲነሳ በርካታ ነገሮችን ያገናዝባል፡፡ ስለምን እንደሚጽፍ፣ ለምን እንደሚጽፍ፣ ለማን እንደሚጽፍ፣ የቃላት አመራራጥ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

ማረው( 2007፣135-136) የመፃፍ ክሂል በባህሪው ክሂሉ ብዙ ነው፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአንቀፅ አመሰራረት፣  የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥ፣የቃላት አጠቃቀም ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚያስፈልጉ ክሂሎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ ክሂሉ እየጻፈ መማርን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቀጥታ ወደ መፃፍ ስራ ከመግባታቸው በፊት በሂደት ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ለአብነት የሚከተሉትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምን እንደሚፃፍ በውል መገንዘብ፣ ርዕስ በርዕስ በመወያየትና በማንበብ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣እንዴት መፃፍና መረጃዎችን እንዴት ማደራጀት እንዳለባቸው የራስ ዕቅድ ማውጣት፣ የመጀመሪያ ረቂቅ መንደፍ፣ ረቂቁን መገምገም፣ መከለስና በርካታ ረቂቆችን በተደጋጋሚ ከተዘጋጁ በኋላ የመጨረሻውን ፅሁፍ መፃፍ ለመጨረሻም ጊዜ እንደገና በጥልቀት አንብቦ መገምገም፡፡

ታደሰ(2007) ፅፈት ማህበረሰብ በይሁንታ የተስማማባቸው ትዕምረቶች ማለትም ፊደላት ተበጅተው ( ተቀርፀው) እየተቀናጁ ለዚህ ተግባር ተብለው በተዘጋጀ ወረቀት፣ ብራና፣ወይም ማንኛውም ጠፍጣፋ ገፅታ ባለው ፅሁፍን በሚቀበል ነገር ላይ ሃሳብን አደራጅቶ ወይም አቀናጅቶ የማስፈር ሂደት ነው፡፡

ፅህፈት ስዕላዊ ትምህርቶችን ፈጥሮ በወረቀት ወይም በሌላ ጠፍጣፋ በሆነ ገፅ ላይ ካማስፈር (ከማስቀመጥ) ይበልጥ ተገላጨን ፅንስ ሃሳብም ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ

የምንፅፋቸው ዓረፍተ ነገሮች እርስ በርሳቸው የሃሳብ ቁርኝት ያላቸው ተጠያቂያዊ የሆኑ፣ፍሰታቸውን የጠበቁ፣ ተለጣጣቂና ወጥነት ያላቸው፣ የቋንቋውን ስርዓት የጠበቁ፣ ጥምር ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ዳግሞ ግዴት ነው፡፡

የጽህፈት ክሂል እንደማናቸውም የተቀሩት ቋንቋ ክሂሎች የራሱ የሆነ የተለየ ባህሪ አለው፡፡ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ሁለቱ ማለትም ማንበብና ማዳመጥ የሌሎችን ስሜት የመቀበልና የመረዳት ሁኔታዎችን ስለሚያሳይ የመረዳት ክሂሎችን/ comprehension skill / ሲባሉ መናገርና መፃፍ ደግሞ ተናጋራው ወይም ፀሃፊው የራሱን ስሜት ለሌሎች ማንፀባረቅ ሁኔታን የሚመለከትባቸው በመሆናቸው የገለፃ ክሂሎች (expression skill) ሊባሉ ይችላሉ፡፡

የመናገር የመፃፍ ክሂሎችን ከተናጋሪው ወይም ከፀሃፊው የሚጠበቁ ውጤቶች መሆናቸው የውጤት ክሂሎች ሊባሉም ይችላሉ፡፡ ፅህፈትና ንግግር አስቀድሞ እንደተገለፀው የውጤት ክሂሎች ቢሆኑም የሚለያዩበት በርካታ ባህሪያት አላቸው፡፡ በፅሁፍ ጊዜ ፅሁፍ አንባቢ ከፀሃፊው ጋር ስለማይገናኝ በፅሁፍ የሚገልፀውን ሃሳብ ወይም መልዕክት ሊያገኝ የሚችለው በተፃፈው ፅሁፍ ምንባብ ውስጥ በሚገኙ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች አማካኝነት ብቻ ነው፡፡ በንግግር ጊዜ ግን የተናጋሪውና የአድማጭ ግንኙነት የተገደበ ስላልሆነ አድማጭ የተናጋሪውን ሃሳብና መልዕክት ይሰማል፡፡ ያልገባውንም በመጠየቅ ከተናጋሪው በሚሰጠው ማብራሪያ የሚተላለፍበትን መልዕክት ምሉዕ ያደርገዋል(ታደሰ፤2007)፡፡

ጽህፈትን እንደ ንግግር ሁሉ በተወለድንበት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ የምናውቀው ወይም በራሱ ዘየን ጠብቆ ቀን ተቆጥሮ የሚመጣ አይደለም፡፡ ነገርግን ጽህፈት የአንድን ቋንቋ የንግግር ድምፆች የሚወክሉ ምልክቶችን በመቅረፅ የቋንቋ ተናጋሪዎች በተስማሙበትና በለመዱት ስርዓት ትርጉም እንዲሰጡ አገጣጥሞ ቃል በመመስረት ቀጥሎም ቃላትን በሀረግ፣ ሀረጋትን በአረፍተ ነገሮች፣ ዓረፍተ ነገሮች በአንቀጽ በማቀናበር የሚካሄድ ክሂል ነው፡፡

ከላይ ምሁራን ስለ ፅህፈት ክሂል ምንነት እንደገለፁት ፅህፈት እንደ ንግግር ክሂል በየአጋጣሚው በፍጥነት የሚለመድ አይደለም፡፡ የጽህፈት ክሂል ለመማር መጀመሪያ የፅህፈት መሳሪያወች ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የፅፈት መሳሪያዎች ከተዘጋጁ በኋላ ሃሳቦችን በማቀናጀትና በማደራጀት ይሰፍራሉ፡፡

አንድን ፅሁፍ በምንፅፍበት ወቅት መጀመሪያ ርዕስ መምረጥ፣ ርዕስ ማጥበብ ወይም መወሰን፣ አስተዋፅኦ (ቢገር) ማዘጋጀት ይጠበቅብናል፡፡ በነደፍነው አስተዋፅኦ መሰረት ስለምንፅፈው ጉዳይ

ሃሳቦችን በማቀናጀት ቅደም ተከተላቸውን በማስያዝ ለአንባቢው ታዋቂ በሆኑ ቋንቋዎች የምንፅፈው ፅሁፍ ነው፡፡

## 2.6 የመፃፍ ችሎታን ማዳበር

ለአንድ ነገር ክህሎት መዳበር ቀድሞ የሚደረግ ልምምድ ውጤት ነው፡፡ የመፃፍ ችሎታን የሚዳብረው ቀድመን በተለያዩ ደራሲያን የተፃፉ ፅሁፎችን ማንበብ አለብን፡፡ ለምሳሌ ልቦለድ ዘወትር የሚያነብ ሰው ታሪኩ በጣም ሲያስደስተው አንባቢውም የመፃፍ ፍላጎቱ እያደረበት እና ለመፃፍ ይነሳሳል፡፡ የመፃፍ ተነሳሽነት እስካለው ድረስ ሁል ጊዜ ፅህፈትን ይለማመዳል ማለት ነው፡፡ሁሉጊዜ የሚፅፍ ከሆነ የሃሳብ አፍላቂ ይሆናል፡፡ ስለሚፅፈው ነገር የሀሳብ እጥረት አይገጥመውም፡፡ ሀሳቡን እያቀናጀ እና ቅደም ተከተሉን አስይዞ የሚፃፍ ከሆነ ፅህፈት እየዳበረ ይመጣል ማለት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡፡

ደረጀ ገብሬ (2013፣174-175) አንብቦ መረዳት እና መፃፍ ቁርኝነታቸው ጥብቅ ነው፡፡ እንደ ማንበብ ክሂል ሁሉ የመፃፍ ክሂል ይሁነኝ ብሎ፣ አቅዶ፣ ቦታና ጊዜ መድቦ፣መሳሪያ አሰናድቶ ተማሪና አስተማሪን አገናኝቶ መስራት ይጠይቃል፡፡ማንበብና መፃፍ እንደማዳመጥና መናገር በቋንቋ ተናጋሪዎች መሀከል በመገኘት እንዳጋጠመ የሚለመዱ አይደሉም፡፡ የተለያየ ጥረት ጠያቂ ክሂሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ክሂሎች ተጠያቂ መሆን ይቻል ዘንድ ልዩ ጥረት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ትጋትና ቁርጠኝነት የሚያሻቸውም እንደሆኑ ባለሙያዎች የሚገልጹትና በትምህረት ቤት ያለፉ ሰዎችም ሁሉ በልምድ የሚያረጋግጡት ተግባር ነው፡፡

ማረው (2007) በበኩላቸው ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ለመለማመድ በሂደቱ ውስጥ ማለፋቸው አንድ አስፈላጊ ነገር ቢሆንም፣ ሌላው አስፈላጊው ጉዳይ ደግሞ የሚለማመዱባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት ነው፡፡ ይህም የመምህሩን ፈጠራ ችሎታን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ለአብነት የሚከተለውን አንዳንድ አማራጭ እንመልከት፡፡ ከአጭር መግለጫ ጋር የአንድት ወጣት ስም ፃፍ፣ ሁለቱ የትና እንዴት እንደሚገናኙ ፃፍ፣ እንደተገናኙ እሱ እሷን ምን ይላታል ? የሚያውቋቸው ሰዎች ምን ይላሉ? በእንዚህ ሂደቶች በማለፍ አንድ አንቀፅ ወይም ከአንቀፅ በላይ የሆነ ድርሰት እንደየ ደረጃው መፃፍ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ በሙህራን እንደተገለፀው አንብቦ መረዳትና መፃፍ ጥብቅ ትስስር ያላቸው መሆኑን፣ ማንበብና መፃፍ እንደ ማዳመጥና መናገር በየ አጋጣሚው የሚለመዱ ክሂሎች አለመሆናቸውን ምሁራን ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ከዚህ በማያያዝ አንብቦ መረዳት መፃፍ ታስቦባቸው ወይም ታቅዶባቸው ቦታና ጊዜ ተመቻችቶላቸው የሚለመዱ ክሂሎች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጫማሪ አንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ክሂል ለማስተማር የመምህራንን የፈጠራ ችሎታንም የሚጠይቁ ናቸው፡፡ መምህራን የፅህፈትን ክሂል የሚያለማምዱ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎችን በፅሁፍ እንዲመልሱ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

በድሉ (2007፣78-80) ተማሪዎች ጥሩ ፅሁፍ የመፃፍ ችሎታ እንዲዳብር በመጀመሪ ፅህፈት በውስጡ የተለያዩ ንኡሳን ተግባራት የያዘ ረጅም ሂደት መሆኑን መገንዘብ አለባቸው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ልምመድም እነዚህን ንኡሳን ተግባራትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በጽህፈት ትምህረት የሚተኮርባቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም ቅድመ ጽህፈት፤ማርቀቅ (drafting)፤ መከለስ ናቸው፡፡ ከላይ በተለያዩ ምሁራን እንደተገለፀው የፅህፈት ክሂል ለማዳበር የተለያዩ ደረጃዎችን መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡ የመጀመሪው ስራ ስለሚፃፈው ርፅሰ ጉዳይ ከአእምሮ የሚፈልገውን ሃሳብ እንደ ወረዳ በወረቀት ላይ መፃፍ ይጠበቃል፡፡ ይህ የሚጠቀመው መጨረሻ ላይ ድርሰቱ ሲፃፍ የሃሳብ እጥረት እንዳይጋጥም ይረዳል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሊከናወን የሚገባው ሃሳብ ከአእምሮ አንደመጣ የተፃፈውን ፅሁፍ ስርዓት በማስያዝ የሚፃፍበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ የፅህፈት ደረጃ የተለያዩ ደራሲያን የፃፉትን ፅሁፍ የሚዳሰስበት ነው፡፡በአራተኛ ደረጃ የሚፃፈው ፅሁፍ የድምፅ፣የቃላት፣የሀረጋት፣የዓረፍት ነገር እና የስርዓተ ነጥብ ስህተት መኖሩንና አለመኖሩን በማረጋገጥ፣ በመከለስ የሚፃፍበት ጊዜ ነው፡፡ ፅሁፉን በስርዓት በማዘጋጀት ለአንባቢው የሚቀርብበት የመጨረሻ የምንፅፈው ፅሁፍ ነው፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች የመፃፍ ችሎታ የሚዳብርበት ሁኔታ አለ፡፡

## 2.7. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅት

በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ያላቸው በመሆኑ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ መጻፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል፤ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱን፣ የታሪክ አወቃቀሩንና የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸው ለሚጽፉት ጽሁፍ ይጠቀሙበታል፡፡ይህም ሂደት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር የሚያመለክት መሆኑን Harp, etal (1996) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡ የሁለቱ በውህደት መቅረብ የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ክሂሎቹ የቀደመ እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸውም እንደሆነ

አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪ May (1990) በተመሳሳይ ተማሪዎቹ ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል።ይህም የሚያሳየው በክሂሎቹ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ያመለክታል።አንባቢዎችና ፀሀፊዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመስታዎት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን የቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው። አንባቢዎችና ፀሀፊዎች ለማንበብና ለመጻፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም 37 ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ።ይኸውም ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፤ፍላጎትም ይኖራቸዋል፤የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤አእምሯዊ ምስል ይፈጥራሉ። የፀሀፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የሁለቱ የመግባቢያ መንገዳቸው የተዘጋጀው በጽሁፍ ነው።የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ ሃሳብ ለመጋራት ወይም ለመዝናናት ጽሁፍ ማግኘት ነው። በመሆኑም ሁለቱም ባለጉዳዮች ማለትም ፀሀፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሁፍ ይገናኛሉ በማለት አስረድተዋል። የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል።የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ገልጸዋል።ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡

## 2.8 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኝው በርካታ የክላስ ድርሳናትን ለመዳሰስ ሞክሯል። ከዚህ ስራ ጋር በተያያዘ ወይም ጥናታዊ ፅሁፍ ርዕስ ዙሪያ ሙህራን የገለፁትን ሃሳብ ለማየት ችሏል። በአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታ አቀናጅቶ ማስተማር በሚለው ዙሪያ ምሁራን ሰፊ ሃሳብ ሰጥተዋል።ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የቀደምት ስራዎችንም ተመልክቷል። የተወሰኑት የቀደምት ስራዎችንም ተመልክቷል። የተወሰኑት የቀደምት ስራዎችንም ሲመለከታቸው ከጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተመሳሳይነት እና ልዩነት ይታይባቸዋል ለአብነት ያህል ከዚህ በታች የተጠቀሱትን እንመልከት፡-

እሸቴ መብራቴ (2003) ማንበብና መፃፍ ክህሎቶችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት ነው። ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የምንባብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹ እንደሚጎለብቱ፣ እሸቴ የመፍትሄ ሃሳብ እንዳስቀመጠው ክሂሎቹን አቀናጅቶ ማስተማር ያለው ጠቀሜታ ተማሪዎች የሚያነቡትን ፅሁፍ ያግዛቸዋል ይላል። ከዚህ በተጨማሪ ማንበብና መፃፍን

በውህደት ማስተማር ትኩረት ተሰጥቶት ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፈል ውጭ ልምምድን እንዲያደርጉ ቢበረታቱ ከሚለው ከዚህ ጥናት ጋር ተማሳሳይነት ሲኖረው፣የእሸቴ ጥናታዊ ፅሁፍ በ2003ዓ.ም የተጠና ሲሆን የዚህ ጥናት ደግሞ የ2015ዓ.ም በመሆኑ ልዩነት አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእሸቴ ጥናታዊ ፅሁፍ የሙከራ ሲሆን የዚህ ጥናት ግና የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና ( በ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ተተኳሪነት ላይ ነው፡፡የመፀሃፉን ይዘት ተንትኖ ማሳየት ስለሆነ ልዩነት አለው፡፡ ከዚህ ባሻገር የእሸቴ (2003) የመጀመሪያ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና፣ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናታዊ ፅፍ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መፅሀፍ ግምገማ ስለሆነ የሰነድ ፍተሻ ብቻ ስለሆነ ልዩነት አለው፡፡

ፍቅሩ ወ/ኪዳን (2008) የቋንቋ ክሂሎችን በማቀናጀት አማረኛን ማስተማር የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማጎልበት ያለው ፋይዳ / አማረኛን እንደሁለተና ቋንቋ በሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት /፡- የቋንቋ ክሂሎችን በማቀናጀት አማረኛን ማስተማር የተማሪዎችን ተግባቦት ብቃት ለማጎልበት የሚቻል ፋይዳ ያለው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት ስለሆነ ተመሳሳይነት አለው፡፡

የፍቅሩ ወልደ ኪዳን (2008) ጥናታዊ ፅሁፍ ከቦታ አንፃር ሲታይ የደቡብ ህዝቦች ክልል የተጠና ሲሆን የዚህ ጥናት ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በማንዱራ ወረዳ የተጠና ጥናት ስለሆነ ከቦታ አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡ የፍቅሩ ወልደ ኪዳን ጥናታዊ ፅሁፍ የሙከራ ምርምር ሲሆን የዚህ ጥናት ደግሞ በ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ የመማሪ መፅሃፍ የይዘት አቀራረብ ትንተና በመሆኑ ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍቅሩ ወልደ ኪዳን ጥናታዊ ፅሁፍ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች በ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ የመማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ተቀናጅተው መቅረባቸውን የዳሰሰ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ የአጠናን ዘዴ በተመለከተ ፍቅሩ ወልደ ኪዳን መጠናዊ የምርምር ዘዴ ሲጠቀም፣ የዚህ ጥናት ፅሁፍ የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን በደጋፊነት መጠናዊ ምርምርን አጥኝው ተጠቅሟል፡፡

እመቤት እሸቴ (2011) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በ2007ዓ.ም ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ ነት የተዘጋጀውን የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ተተኳሪነት ነው፡፡ የዚህ ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2015ዓ.ም የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና ላይ የተሰራ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ በተመለከተ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የሚከተል ሲሆን በደጋፊነት

መጠናዊ ምርምርን ተጠቅሟል፡፡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፣የመማሪያ መጽሀፉ አቀራረብ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በተቀናጀ መልኩ እንደተዘጋጁና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር እገዛ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ሁኔታዎች ሁለቱ ጥናታዊ ፅሁፍ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከቦታ አኳያ የእመቤት እሸቴ ጥናታዊ ፅሁፍ የተካሄደበት አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ በህዳሴ በጎሮ፣በቦሌ፣ለሚ እና በምስራቅ ቀጥር ሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርተ ቤቶች ላይ የተደረገ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ነው፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያወችን በተመለከተ እመቤት እሸቴ የተጠቀመችባቸው ሰነድ ፍተሸ፣ ምልከታ፣ የፅሁፍመጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ፤ የዚህ ጥናት አድራጊ የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰነድ ፍተሸ እና ምልከታ ነው፡፡ በመሆኑም ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡

ነብዩ ነጋሽ ( 2005) በግጥም አማካይነት በአማረኛ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታን ማዳበር፣ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት በደንበጫ ከፍተኛ ትምህረት መሰናዶ እና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ነብዩ ያስቀመጠው አስተያየት የቋንቋ መልመጃዎችን የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብሩና ለሚያጋጥሟቸው ስነ ፅሁፋዊ መልመጃዎችን በደንብ የሚያዘጋጃቸው ሆነው ሊዘጋጁ ይገባል በማለት ሀሳቡን አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ደግሞ በ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉትን ይዘቶችና መልመጃዎች የአንብቦ መረዳትና የፅሁፍ ችሎታን አቀናጅቶ ለማቅረብ ብቃት ያላቸው መሆኑን የተመለከተ ስለሆነ ተመሳሳይነት አለው፡፡

የነብዩ ጋሹ ጥናታዊ ፅሁፍ በ2005 ዓ.ም የተሰራ ሲሆን፣ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን በ2015ዓ.ም ነው፡፡ የነብዩ ጥናት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማረኛ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር ግጥም ያለው ሚና በሙከራ ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን በ8ኛ ክፍል 2015 ዓ.ም በአዲሱ የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የአንብቦ

መረዳትና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶችና መልመጃዎችን መተንተን ስለሆነ ልዩነት አላቸው፡፡

ትዝታ ደሳለኝ (2003) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናት ውጤትም ክሂሎችን አቀናጅተው የሚያቀርቡ ጥቂት መምህራንና ክሂሎችን አቀናጅቶ የማያቀርቡ በርካታ መምህራን እንዳሉ የታወቀ ሲሆን የተማሪዎቹም የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀባበል ጥሩና መጥፎ መሆን እንደ መምህራኑ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ጥሩና መጥፎ መሆን የተወሰነ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት:-የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ምእራፍ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት የጥናቱ ዘዴዎች ቀርበዋል። በጥናቱ ተተኳሪ የሚሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነት፣የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ፣የጥናቱ አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርበዋል።

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በ2015ዓ.ም አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የተጠና ሲሆን፣ ከርዕሱ አንፃር አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ተተኳሪነት ላይ። በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው የአጠናን ዘዴ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን በዋናነት አይነታዊ ምርምር እና በደጋፊነት መጠናዊ ምርምር አገልግሎት ላይ ውሏል። በዚህ ጥናት ቅይጥ የምርምር ዘዴ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በገለጻ እና በቁጥር መረጃ ትንተና ስለሆነ ነው። በመሆኑም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የጥናቱ አቀራረብ ገላጭ ስልትን የተከተለ በመሆኑ ነው። አጥኚው በተጠቀሰው መጽሀፍ ላይ እንዲሁም የክፍል ውስጥ አተገባበሩ ላይ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ለግምገማው በሚዘጋጁት መስፈርቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በአይነት በአይነት በማድረግ መተንተን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኝውም በቁጥር ለምትገልጸው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡ በመሆኑም በጥናቱ ቅይጥ የምርምር ዘዴን የሚከተለውን Cresswell,(2009) እና የያለው (2001) የምርምር መጻህፍት ለጥናቱ መነሻ በግብዓትነት አገልግሎት ላይ ውለዋል።

### 3.2. የጥናቱ አቀራረብ

ጥናታዊ ፅሁፍ ተግባር ላይ የዋለው የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን፣ በቁጥር የተገለፁት መረጃዎች ለመተንተን በደጋፊነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል። ያለው ዕንዳወቅ (2006፣20) በምርምር ሂደት ሁሉም ነገሮች በቁጥር የሚገለፁ ወይም የሚወከሉ አይደሉም። ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገው ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በአይነት የሚገልፅ ይሆናል። ስለዚህ በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች ሁሉም

በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልዩነት አላቸው ብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በስታስቲካዊ ዘዴ አይገልፃቸውም፡፡ መረጃዎችን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለፃው መንገድ ተከትሎ ነው፡፡ ከላይ ሙህራን እንደገለፁት አይነታዊ ምርምር ዘዴን ለመጠቀም የተፈለገበት የተጠናው ጥናት የቀረበው ገላጭ ስልትን በመጠቀም ነው፡፡መጠናዊ ምርምር በቁጥር መረጃ አተናተን ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አጥኝው መጠናዊ ምርምርን በአጋዥነት ተጠቅሟል፡፡

## 3.3. የጥናታዊ ፅሁፉ የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጭ ቀዳማይና ደህራይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በ2015 ዓ.ም የታተመው የ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ነው፡፡  ከዚህ በተጨማሪ የመረጃ ምንጩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው ፡፡መማሪያ መጽሀፍ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መገምገም በመሆኑ ነው፡፡  የተገኙትን መረጃዎች በአይነታዊ የምርምር ዘዴና በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ተተንትኗል፡፡ የመረጃ ምንጮችን በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-

ያለው እንዳወቅ( 2006) የሰውን ባህሪ ለመለካት የምንጠቀምባቸውን ዋና መሳሪያዎች ቃላት ናቸው፡፡ ሰዎች የሚሏቸውን ነገሮችና የሚያሳያቸውን ድርጊቶች መሰረት በማድረግ በቃላት አማካኝነት የባህሪያቸውን አይነት ለመግለፅ ተሞክሯል ፡፡ ይህንን ማድረጋችን በግርድፉም ቢሆን የባህሪ ልኬት እያወጣን ነው፡፡ ስለሆነም የምንጠቀምባቸው ቃለት ለመረጃው ትክክለኝነት ከስኳሩ ሚዛን ይበልጥ እጅግ ወሳኝ ናቸው፡፡ በዋሾ ሚዘን የሚለካ ስኳርም ሆነ ጨው መጠኑ ትክክል እንደማይሆን ሁሉም በተገቢው ሁኔታ ባልተዘጋጀ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃም እንደዚሁ ነው፡፡ ይላሉ  ከላይ ያለው እንደገለፀው የመረጃ ሰጭዎችን ሃሳብ በታማኝነት ወይም በትክክለኛው መንገድ ማስቀመጥና መተንተን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ያለው እንዳወቅ በምሳሌ እንዳስቀመጡት በውሸት መረጃዎች የተጠና ጥናት ውጤቱም ፋይዳ የሌለው ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም አንድ ጥናት አድራጊ የሰበሰበውን መረጃ በትክክል ማስቀመጥ እንዳለብን ይጠበቃል፡፡

## 3.4. ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግብአት ያስገኛል ተብሎ የታሰበው በቤኒሻንጉል ክልል በ2015ዓ.ም የታተመው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተማሪው መፅሀፍ ሲሆን ፣በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ተመርጧል ፡፡ከዚህ በተጨማሪ የማንዱራ፣የጉማዲ፣ የማንጃሪ

፣የግልገልበለስ እና የኤዲዳ 8ኛ የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን በአመቺ የናሙና አመራረጥ ተመርጠዋል ። በመሆኑም ከብዙዎቹ ውስጥ በናሙና አመራረጥ ዘዴ ጥቂቶችን ይመርጣል ማለት ነው ።ይህ ጥናት አንድ መፅሐፍ ብቻ ይዘቶችንና መልመጃዎችን የሚገመግም በመሆኑ መምህራን ለመፅሀፍ ግምገማው ተመርጧል።

ያለው እንደወቅ (2006) እንዳስቀመጡት ናሙና ስንል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባት በሙሉ በመውሰድ በጥናታችን ተሳታፊ ለማድረግ ሳንችል ስንቀር ወይም ማሳተፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር፣ነገር ግን አጠቃላዩን ብንወስድ ልናገኝ እንችላለን ብለን የምናስበውን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ (ነገሮችን) ስርዓታዊና ተጠየቃዊ መንገዶችን በመከተል መርጠን በጥናታችን እንዲካተቱና መረጃ እንዲሰጡን የምናደርጋቸው የጥናቱ አካላይ ውስን ክፍል ናቸው።

ከላይ ያለው እንደገለፁት ለጥናታዊ ፅሑፍ መረጃ መሠብሰብ ግዴታ ነው። በመሆኑም መረጃውን ለመሠብሰብ ከቁጥራቸው ብዛት አንፃር አስቸጋሪ ይሆናል። ከዚህ የተነሳ በርካታ ቁጥር ካላቸው ሰዎች ወይም ነገሮች ናሙና መምረጥ ይጠበቅብናል። ናሙና ለመምረጥ የተለያዩ የመምረጫ ዘዴዎችን እንጠቀማለን።

## 3.4.1 የጥናቱ ክልል አመራረጥ

አጥኚው የሚኖረው በቤኒሻንጉል ክልል፣መተከል ዞን፣በማንዱራ ወረዳ ውስጥ ነው። በመሆኑም መረጃዎችን በቅርበተ አገኛለሁ ብሉ በማሰብ ይህንን ክልል በአመቺ የናሙና ዘዴ (Convenience sampling method) መርጧል።

## 3.4.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ቀደም ባሉት ዓመታት ስራ ላይ ውሎ የነበረው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ በተለያዩ አጥኝዎች ተጠንቶ ችግሮች ወጥተዋል። አጥኚውም በዚህ የክፍል ደረጃ በሚያስተምርበት ወቅት ችግሮችን ለመመልከት እድል ስለነበረው ለጥናቱ ተመራጭ የክፍል ደረጃ ሆኗል። በተጨማሪም ይህ አጋጣሚ አጥኚውም ስለመፅሐፉ ዕውቅና እንዲኖረው አድርጓል። በመሆኑም በመፅሐፍ ውስጥ የነበሩት ይዘቶች ችግር አዲስ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ምን ያህል መሻሻል እንዳሳየ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዓላማ ተኮር የናሙና ስልት በመምረጥ ጥናት ላይ ውሏል። ያለው(2006) ዓላማ ተኮር ናሙና /purposeful, puroosive Judgment, or sudgmental sampling/ በዚህ የናሙና ዘዴ

ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመረጡት ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው ። እነማንን ብመርጥ የሚፈለገውን መረጃ ኖሯቸው ይሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፍ አሰፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ይመርጣል።

ያለው እንደገለፁት አጥኚው የ8ኛ ክፍል የመረጠበት ምክንያት ከጥናቱ ርዕሰ ጋር በተያያዘ ሆኖ ከዚህ ጥናታዊ ርዕሰ መረጃ የሚገኝው ከየት ነው ። የሚለውን ጥያቄ አጥኚው በመመለሰ በዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴ የ8ኛ ክፍልን በመምረጥ ጥናቱ ተካሔዷል ።

### 3.4.3 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለጥናቱ ያመቸኛል ያላችን ትምህርት ቤቶች መርጧል። የተመረጡት ት/ቤቶች ማንዱራ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ማንጃሪ፣ ኤዲዳ፣ ግልገል በለስ እና ጉማዲ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ለጥናቱ ውለዋል።

### 3.4.4 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ናሙና አመራረጥ

ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተተኳሪውን መጽሐፍ ሲያስተምሩ የቆዩ አሁንም በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን አጥኚው በቅርበት ተገኝተው መረጃ ይሰጡኛል ያላቸውን መምህራን በአመቺ የናሙና ዘዴ በመምረጥ መረጃ ሰብስቧል።

#### 3.4.4.1 ቃለ መጠይቅ

የተደረጉላቸው መምህራን ዳራ

| ተ.ቁ | ዕድሜ | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የት/ቤቱ ስም | የሰለጠነበት የት/ት አይነት | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 33 | ወ | ዲግሪ | ኤዲዳ | አማርኛ | 13 ዓመት |
| 2 | 42 | ወ | ዲግሪ | ማንዱራ | አማርኛ | 20 ዓመት |
| 3 | 51 | ወ | ዲግሪ | ግልገል በለስ | አማርኛ | 31 ዓመት |
| 4 | 30 | ሴ | ዲፕሎማ | ጉማድ | አማርኛ | 3 ዓመት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | 28 | ሴ | ዲፕሎማ | ማንጃሪ | አማርኛ | 10 ዓመት |

## 3.5. የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴዎች/መሳሪያዎች /

የመረጃ መሠብሰቢያ መሳሪያዎች በርካታ ቢሆኑም እንደ ጥናቱ ዓይነት ሁሉንም መጠቀም ላያስፈልግ ይችላል ፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ አዲስ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ማየት ወይም መተንተን በመሆኑ ለዚህ ጥናት የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያ የሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

ያለው (2006፣147)የምርመር ውጤቶች በመረጃ ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መረጃዎቹ ደግሞ በመሠብሰቢያዎቹ ላይ፡፡ የምርምር ውጤቶች ለፓሊሰና የተለያዩ ውሳኔዎች መሠረት ናቸው፡፡ የፓሊሰ ውሳኔውች ጥንካሬና ድከመት ደግሞ በምርምር ውጤቶች ላይ በእጅጉ ይወሰናል፡፡የፓሊሲ ውሳኔዎች በምርምር ውጤቶች፣የምርምሩ ውጤቶች በመረጃ ፣መረጃዎች ደግሞ በመሠብሰቢያ ዘዴዎች የሚደገፍ ከሆነ የዚህ ሁሉ መሠረቱ መለኪያዎቹ ናቸው ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደምሁራን ገለፃ የመረጃ መሠብሰቢያ መሳሪያዎች ለአንድ ምርምር  መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡ ምርምሩ በጥሩ መረጃ ወይም በትክክለኛ መረጃ ካልተደገፈ ግብ መቺ ወይም ውጤቱ አስተማማኝ አይሆንም፡፡

### 3.5.1 የሰነድ ፍተሸ/ documents /

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አንብቦ መረዳትና የመፅሀፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በመሆኑ ዓላማው መፅሀፍ መገምገምንም ነው፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ በማደራጀት በመተንተን ለጥናቱ ስራ ላይ ውሏል፡፡

### 3.5.2. ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥንታዊ ፅሁፍ በሁለተኛነት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ በመሆን አግልግሎት ላይ የዋለው ቃለ መጠይቅ ነው ፡፡ቃለመጠይቅ አጥኚው ለጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ ይሰጡኛል ብሎ በናሙና የተመረጡትን መምህራን ፊት ለፊት በማግኘት መረጃ ሰብስቧል ፡፡ለዚህም በአመቺ ናሙና የአመራረጥ ዘዴ የአምስቱን ትምህርት ቤቶች ማለትም የማንዱራ ፣ማንጃሪ፣ኤዲዳ፣ግልገልበለስ እና ጉማዲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን

ስድስት ጥያቄዎች ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው የየግላቸውን ለጥናታዊ ፅሁፍ መልስ ሰጥተዋል ::

### 3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መፅሀፍ መገምገም በመሆኑ የሰነድ ፍተሸ ዋና ዓላማም ለጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው በመረጠው የ8ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ በጥልቀት መመልከት ይሆናል።በመሆኑም በመዛግብት ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በሀተታ የተሰበሰበው በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ በገለፃ ተተንትኗል።ከዚህ በተጨማሪ በቁጥር የተገኙት መረጃዎች በደጋፊነት መጠናዊ የትንተና ዘዴ በቁጥር እና በፐርሰንት መረጃዎች ተተንትነዋል ::

## ምዕራፍ አራት:-የመረጃ ትንተና

ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሶስት ለመግልፅ እንደተሞከረው ጥናት የተደርገው በ2015 ዓ'ም ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ የዋለውን የመማርያ መፅሐፍ ላይ ተካሄዷል። ጥናቱም የተመለከተው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የአምብቦ መረዳትና የፅህፈት ክሂሎች በማቀናጀት መቅረባቸውን መተንተን ነው። አጥኝው ለ8ኛ ክፍል 2015 ዓ.ም አገልግሎት ላይ የዋለው የተማሪውየመማርያ መፅሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሀ ትምህርት በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በ2015 ዓ.ም አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል ማስተማርያ መፅሀፍት ከማውጫው ላይ እንደገለፀው 288 ገፅ ያለው ነው። በሌላ በኩል መፅሀፉ በአስራ ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ አስር ዋና ርዕሶች ሲኖሩት፣ ንዑስ ርዕሶች ደግሞ ሀያ ሶስት ናቸው። ከሰነድ ፍተሸ እና በምልከታ የተገኙት ውጤቶች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

## 4.1 የመመሪያ መፅሃፉ ያከተታቸው ዋና እና ንዑስ ርዕሶች

ሰንጠረዥ አንድ የመማሪያ መፅሀፉ በውስጡ የያዛቸው አብይ እና ንዑስ ርዕሶች

| ተ.ቁ | ምዕራፍ | ዋና ርዕሶች | ንዑስ ርዕሶች |
|---|---|---|---|
| 1 | አንድ | ስራና የስራ ስነመግባር | -ሰው መሆን<br>-በላይ ዘለቀ<br>-የበላይ ዘለቀ አጭር የህይወት ታሪክ |
| 2 | ሁለት | ባህላዊ ቅርሶች | -ሉሲ<br>-ባህልና ቅርስ<br>-ምግብና መጠጥ<br>ንባብ |
| 3 | ሦስት | ሰብዓዊ እሴቶች | -ተንኮለኛው ነብር<br>-የአረጋዊያን ቀን |
| 4 | አራት | አጭር ልብወለድ | -የበይወች አለመስማማት ለተበይወች ይበጃል<br>-የካቲት 12 ቀን<br>የአጭር ልብወለድ አላባውያን |
| 5 | አምስት | ህዝብ | የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልህዝብ |
| 6 | ስድስት | በረሃማነት | የህዳሴው ግድብ ጉብኝት |
| 7 | ሰባት | የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ | -የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስኤዎች እና ችግሮቻቸው<br>-እያ ጥበቡ |
| 8 | ስምንት | ሰላም | ዘይነባ |
| 9 | ምዕራፍ ዘጠኝ | የአየር ንብረት | -ሰው መሆን<br>-የአየር ንብረት<br>-የሸማቾች ማህበር<br>-የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔዎች |
| 10 | አስር | ተውኔት | -የትያትር (የተውኔት ጥበባት<br>-ታማኝነት<br>ልጄ ልጄ ባይ |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተገለፀው የመማሪያ መፅሃፉ ዋና እና ንዑስ ርዕሶችን የያዘ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ምዕራፍ ሁለት፣ ምዕራፍ አራት እና ምዕራፍ ዘጠኝ አንድ አንድ አብይ ርዕስ ሲኖራቸው፣ በየምዕራፉ የቀረቡ ንዑሳን ርዕሶች አራት አራት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምዕራፍ አንድ፣ ምዕራፍ ሰባት እና ምዕራፍ አስር አንድ አንድ ዋና ርዕስ ሲኖራቸው፣ በየእያንዳንዱ ምዕራፍ ሦስት ሦስት ንዑሳን ርዕሶችን አካተዋል፡፡ በመጨረሻም ምዕራፍ ሦስት፣ አንድ አብይ ርዕስ ሲኖረው፣ ሁለት ንዑስ ርዕሶችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ስድስት እና ምዕራፍ አምስት አንድ አንድ ዋና ርዕሶች ሲኖራቸው፣ ንዑስ ርዕስም አንድ አንድ አላቸው፡፡ በ2015 ዓ.ም ተግባር ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መፅሃፍ አጠቃላይ ያካተታቸው ርዕሶች ሲታዩ አስር ዋና ዋና ርዕሶች ሲኖሩት፣ በነዚህ ዋና ርዕሶች ውስጥ የሚካተቱ ንዑሳን ርዕሶች ሃያ ሶስት አሉት፡፡

## 4.2 ለአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡ ጥያቄዎች ዓይነት

ሰንጠረዥ ሁለት በመፅሃፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ተዘጋጅተው የቀረቡ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | ምዕራፍ | ርዕስ | የጥያቄዎች አይነት | | | | የጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዝግ ጥያቄዎች | | | ክፍት ጥያቄዎች | |
| | | | አ/ሀ | ምርጫ | አዛምድ | | |
| 1 | አንድ | ስራና የስር ስነመግባር | -------- | -------- | 11 | 8 | 19 |
| 2 | ሁለት | ባህላዊ ቅርሶች | 5 | -------- | -------- | 16 | 21 |
| 3 | ሦስት | ሰብዓዊ እሴቶች | -------- | -------- | -------- | 7 | 7 |
| 4 | አራት | አጭር ልብወለድ | -------- | -------- | 15 | 5 | 20 |
| 5 | አምስት | ህዝብ | 6 | -------- | -------- | -------- | 6 |
| 6 | ስድስት | በረሃማነት | 6 | -------- | 6 | 13 | 25 |
| 7 | ሰባት | የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ | 5 | 8 | -------- | 7 | 20 |
| 8 | ስምንት | ሰላም | -------- | -------- | 6 | 11 | 17 |
| 9 | ዘጠኝ | የአየር ንብረት | -------- | -------- | 14 | 6 | 20 |
| 10 | አስር | ተውኔት | -------- | -------- | 7 | 16 | 23 |
| | | ጠቅላላ ድምር | 22 | 8 | 59 | 89 | 178 |
| | | ፐርሰንት | 12.3% | 4.4% | 33.1% | 50% | 100% |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከቀርቡት መልመጃዎች የክፍት ጥያቄዎች ብዛት በቁጥር ሲገለፅ 89 ሲቀርቡ  በፐርስንት 50%ሲሆኑ ፣ በዝግ ከቀረቡት ውስጥ እውነት ወይም ሀሰት የቀረቡት ጥያቂዎች ብዛት በቁጥር 22 በፐርሰንት 12.3% ሲሆኑ ፣ በምርጫ የቀረቡት  ጥያቄዎች ብዛት በቁጥር 8 በፐርሰንት 4.4% ነው፡፡ በአዛምድ የቀረቡት ጥያቄዎች ብዛት 59 በፐርሰት ደግሞ 33.1% ቀርብዋል፡፡

በዚህ የጥያቄዎች ትንተና እንደሚያሳየው አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡት ጥያቄዎች 89 ወይም 50% የያዘው ክፍት ጥያቄዎች በመሆናቸው አንብቦ መረዳት ለማስተማር በአብዛኛው ይህን የጥያቄ አይነት  መፅሐፉ አካቷል፡፡ ከክፍት አጠያየቅ በቀጣይነት ደረጃ የያዘ አዛምድ ጥያቄዎች ናቸ ው፡፡ በሶስትኛ ደረጃ የተቀመጠው ወይም የጥያቄዎች አይነት ብዛት ሶስተኛ ደረጃ የሆነው እውነት /ሀሰት አጠያየቅነው፡፡ ይኸውም የጥያቄ ብዛት 22(12.3%) በመሆኑ ከክፍት ጥያቄዎች እና ከአዛምድ ጥያቄዎች በቀጣይነት ደረጃ የያዘ ነው፡፡ በመጨረሻ ለአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበው የጥያቄ አይነት  የምርጫ ጥያቄ ነው፡፡ በምርጫ አይነት የቀረቡ 8 (4.4%) ሲሆኑ ፣ ከክፍት ጥያቄዎ ች አንፃር ሲነፃፀር አንብቦ መረዳት በምርጫ ጥያቄ ለማስተማር ዝቀተኛ ቁጥር የተሰጠው በመሆኑ ትኩረት አልተሰጠውም፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ለክፍት የአጠያየቅ አይነት ትኩረት መስጠት ገደብ የለሽ በመሆኑ አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በተለያየ አቅጣጫ ያቀርቡታል፡፡ ተማሪዎች የሀሳብ አፍላቂ በመሆን መልመጃዎችን በሰፊው አብራርተው ያቀርባሉ፡፡

## 4.3. በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የትእዛዞች አቀራረብ ትንተና

ሰንጠረዥ ሶስት ፦አንብቦ መረዳት ለማስተማር መልመጃዎችን ለመስራት የትእዛዞች ሁኔታ ትንተና

| | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መልመጃዎች የሚመለሱበት የትዕዛዞች ዓይነት | የትዕዛዞች ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|
| 1 | በቃል እንዲመለሱ የሚያደርጉ ትዕዛዞች | 2 | 6% |
| 2 | መልመጃዎች በፅሁፍ እንዲመለሱ የሚገልፁ ትእዛዞች | 16 | 48.4% |
| 3 | መልመጃዎች በቃል ወይም በፅሁፍ በምን ሁኔታ እንደሚመለሱ የማይገልፅ ትዕዛዝ | 15 | 45.4% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ ድምር | 33 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተቀመጠው አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ የሚገልፁ ትእዛዞች 2(6%)፣የቀረቡትን ይዘቶች በፅሑፍ እንድመልሱ የሚገልፁ ትዕዛዞች ብዛት 16(48.4%) ሲሆኑ፣ በቃል ወይም በፅሑፍ ተማሪዎች መልመጃዎችን ለመስራት ግልፅ ያልሆኑ ትዕዛዞች ብዛት 15(45.4%) ናቸው ። ይህ የሚያሳየው በአብዛኛው የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች በፅሑፍ እንዲመለሱ የተደረገ ሲሆን ፣በቃል እንዲመለሱ የተደረጉ መልመጃዎች ብዛት ዝቅተኛ ነው። በመጨረሻም አንብቦ መረዳት ለማስተማር ከቀረቡት ትዕዛዞች ብዛት 15 (45.4) ግልፅነት የሌላቸው ናቸው። ይኸውም ተማሪዎችን ግራ የሚያጋባ ነው።

## 4.4 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና

1. **ቅድመ ንባብ መልመጃዎች**፦ተማሪዎች ንባቡን ከማንበባቸው በፊት ያላቸውን የቅድመ ዕውቅት ለመፈተሽ ቅድመ ጥያቄ ቀርቧል ።ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ምንባቡ ስለምን ጉዳይ የሚያትት እንደሆ ነ ግምት የሚሰጥበት ተግባር ነው።

2. **የንባብ ተግባራት**፦ተማሪዎች በንቃተ ህሊና ለምንባቡ ትኩረት በመስጠት የደራሲውን ሀሳብ ወይም መልዕክት የሚረዱበት ጊዜ ነው ። በሌላ በኩል ለሚያጋጥማቸው አዳዲስ ቃላት በምንባቡ አውድ መሰረት ፍቻቸውን በመስጠት ሀሳቡን የሚረዱበት ተግባር ነው።

3. **ድህረ ንባብ ተግባራት**፦ተማሪዎች የንባቡን ሀሳብ መረዳትና አለመረዳታቸውን የሚገመገሙበት ወቅት ነው። በ8ኛ ክፍል በ2015 ዓ'ም ለመማር ማስተማ የተዘጋጀው መፅሐፍ ውስጥ ከዋና ርዕሶችና ከንዑሳን ርዕሶች ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ተካተዋል። ምሳሌ ፦ምዕራፍ አንድ <<ስራና የስራ ስነ ምግባር >>በሚለው ርዕስ የቀረቡ ጥያቄዎች

ሀ.ቀላል ስራ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ከባድ ስራ ማለት ምን ማለት ነው ? የመሳሰሉት ቀርበዋል።ከዚህ በላይ ለማሳያነት ከመፅሐፉ ውስጥ ለመማሪያ ተግባር የቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎችን አእምሮ የሚያነቃቁ፣ ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር ለማያያዝ የሚያስችሉ ናቸው። የቀርቡት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ምንባቡ ስለ ምን ጉዳይ ለማንሳት እንደሚሞክር ግምት ለመስጠት የሚያስቸግር ሁኔታ

አይኖርም ። በቅድመ ንባብ  የቀረቡ መልመጃዎች የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማነሳሳት ብቁነት ያላቸው ናቸው ።

በሁለተኛ ደረጃ የምናየው በ2015 ዓ.ም በ8ኛ ክፍል  አማርኛ ቋንቋ ለማስተማርያነት አዲስ ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ የዋለው መፅሐፍ ፤የንባብ  ጊዜ ተግባራትን ለማየት እንሞክራለን  ። የንባብጊዜ ተግባራት ተማሪዎች በክፍል ውስጥፀጥታ ሰፍኖ  ለንባብ ስሜታቸውን የሚሰጡበት ጊዜ ነው ። ምሳሌ ፦ ምዕራፍ ሁለት<< ባህልና ቅርስ >>የሚለው ርዕስ ንባቡን በግላችሁ ድምፅ ሳያሰሙ ፣ የከንፈር እንቅስቃሴ ሳያደርጉ ፣ ፅሑፉን በጣታቸው ሳይጠቁሙ ፣ አይናቸውን በማንቀሳቀስ እንዲያነቡ ይምከሯቸው ። ይህንን በማድረጋቸው በፍጥነት ለማንበብ እንደሚረዳቸው ያስገንዝቧቸው። ንባቡን እያነበቡ መሀል ሲደርሱ የንባብ ጊዜ ጥያቄ እንደሚያጋጥማቸው እና ንባባቸውን ገትተው ለቀረቡላቸው ጥያቄሪዎች መልስ ነው  የሚስቱን በማስታውሻ ደብተራቸው እንዲፅፍ ይምከሯቸው ። ተግባራቱንም ይከታተሉ ። ከዚያም ወደ ንባባቸው እንዲመለሱ ይግለፁላቸው ።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ማድረግ ያለባቸውን እና ማድረግ የሌለባቸ ውን ይመክራል ። በንባብ ጊዜ አዕምሮን የሚረብሹ ድምፆች ወይም ሌሎች ነገሮች መከናወን የለባቸውም ።ተማሪዎች ፅሑፉን በስርአት በማንበብ እና ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታዎሻ እንዲያሰፍሩ ተ ደርጓል ። የንባብጊዜ ጥያቄዎችን ከመለሱ በኋላ ወደ  ምንባባቸው እንዲመለሱ ሆኗል።

ሶስትኛ ተግባር ፤ዲህረ ንባብ ተግባር ነው ። ይህ ተግባር ከቀረበው ንባብ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው  አንባቢው የሚፈተሽበት ነው ።

ለምሳሌ፦ በመማሪያ መፅሐፉ የቀረበው <<ባህላዊ ቅርሶች >>ከሚለው ርዕስ ድህረ ንባብ ተግባር ተማሪዎች አንብበው እንደጨረሱ  በቅድመ ንባብና በንባብ ጊዜ ለቀረቡ ጥያቄዎች የሰጧቸውን መልሶች ከንባቡ ፍሬ ሀሳብ ጋር ያለውን ተዛምዶ እንዲያገናዝቡ ጊዜ ይስጧቸው ። ከዚያም በግንዛቢያቸው መሰረት ለጥያቄዎቹ የሰጡትን መልስ ካነበቡት ጋር ያለውን ተዛምዶና ልዩነት እጅ አውጥው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው  /8ኛ ክፍል የመምህሩ መማሪያ መፅሐፍ/

ከላይ በመምህሩ መማሪያ ላይ የሰፈረውን ለምሳሌ ተቀንጭቦ እንደተገለፀው የድህረ ንባብ ተግባራት በመማሪያ መፅሐፉ  ውስጥ ቀደም ብለው በተከናወኑ የንባብ ተግባራት መረጃዎች የሰጡአቸውን መልሶች ከምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ጋር የሚያገናኙበት ሁኔታ ተገልጿል። ይሄውም ያለውን አንድነት እና ልዩነት የሚመሳከርበት ተግባር ነው።

## 4.5. በመፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የቀረበ የይዘት ትንተና

የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ሲዘጋጁ ተማሪዎችን ታሳቢ በማድረግ ሁኔታ ነው የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎችን እድሜ የሚመጥን ከሆነ ፣ የክፍል ደረጃዎችን የሚቃኝ ፣ የተማሪዎችን አካባቢያዊ ሁኔታ የተገነዘበ ከሆነ ለተማሪዎች ጥሩ ይዘቶች ተዘጋጅቶ ቀርቦላቸዋል ያስብላል ፡፡

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ይዘቶች ፣

* ምዕራፍ አንድ <<ስራና የስራ ስነምግባር ትዕዛዝ1 ፦ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመውያየት በቃል መልስ ስጡ ፡፡

ሀ . ጥሩ ስነ ምግባር የሚባሉት ምንምን ናቸው ?

ለ. የመጥፎ ስነ ምግባር መስፈርቶችን ግለፁ፡፡ ሌሎችም ተካተዋል፦ ምዕራፍ ሁለት << ባህላዊ ቅርሶች >>(ገፅ12) ትዕዛዝ አንድ ፦ ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ ፡፡

ሀ . ባህልና ቅርስ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ለ. የቅርስ ፋይዳዎችንም ምረጡ ፡፡

ሐ. የባህልና ተፈጥሯዊ ቅርሶች አንድነትና ልዩነት አብራሩ፡፡ ሌሉችም ይገኛሉ፡፡

ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ የቀረቡት ይዘቶች ስንመለከታቸው ለክሂሉ ትኩረት ተደርጎበታል ፡፡ይዘቶቹ ከተማሪዎች እለት ከእለት ህይወት ጋር ወይም የሚገናኝ ፣ የቀደመ ዕውቀታቸው የሚቃኝ ተማሪዎችን ግምት ውስጥ ያስገባነው ፡፡ ይህ ሲባል የተዘጋጁት ይዘቶች የተማሪዎችን አካባቢያዊ ሁኔታ የቃኘ ነው ፡፡ይዘቶቹ አካባቢያዊ በመሆናቸው ለመረዳት ችግር አያጋጥማቸውም ፡፡ከዚህ በተጨማሪ የቀረቡት ይዘቶች በዝግና እና በክፍት አጠያየቅ የቀረቡ በመሆኑ ፣ በክፍት የቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎች ሀሳብ አፍላቂ እንዲሆኑ ለሀሳባቸው ማብራሪያ እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ናቸው ፡፡ በዝግ አጠያየቅ አይነት የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ ተማሪው ንባቡን አንብቦ የተረዳውን ወይም በአዕምሮው የያዘውን ሀሳብ የሚገልፁት ነው፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ሌላው የተካተቱ ይዘቶች

ምዕራፍ አራት << አጭር ልቦለድ >> (ገጽ 62) አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበ ርዕስ የካቲት 12 ቀን ትዕዛዝ አንድ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ ፡፡

ሀ.የልቦለዱ ባለታሪኮች እነማን ናቸው ?

ለ.የአቶ እውነቱን ገጽታ ግለፁ። እና ሌሎችም ይካተታሉ ።

ትዕዛዝ ሁለት ፦ በ"ሀ" ስር ለተደረደሩት ቃላት በ"ለ" ስር ከተዘረዘሩት ጋር በተመሳሳይ አዛምዱ

ምዕራፍ አምስት ፦<<ህዝብ>> ገፅ75 አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበ ርዕስ <<የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝብ>> ትዕዛዝ አንድ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት የሆነውን ትክክል ውሸት የሆነውን ስህተት በማለት መልሱ ።

ሀ.የክልላችን የህዝብ ቁጥር በፍጥነት እያደገ ነው ።

ለ.የክልላችን ነባር ብሔረሰብ ባብዛሀኛው በንግድ ስራ ይተዳደራል ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ይዘቶች ከቀረበላቸው ቅንጫቢ ፅሁፍ ተማሪዎች አንብበው ሀሳቡን በመረዳት በምንባቡ መሰረት የተዘጋጁትን መልመጃዎች የሚሰሩበት ሁኔታ ነው። ከቀረበላቸው የማስተማሪያ ይዘት መሰረት ተማሪዎች የፈጠራ ስራ ወይም የስነ ፅሁፍ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ይዘት ተካቷል፦ከዚህ ባሻገር የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎችን አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ተማሪው ይዘቱን ከአካባቢው ጋር በማገናዘብ አንብቦ እንዲረዳተዘጋጅቶ የቀረበ ይዘት ነው። በዚህ ይዘት የቀረቡት ተማሪው አንድን ሀሳብአብራርቶ ወይም ግልፅ አድርጎ ለማሳየት ወይም የሀሳብ አፍላቂ እንዲሆን በተደረገ መልኩ ይዘቶች ቀርበዋል። ተማሪው የአንድን ነገር ውጤት የሚኖረው ከኋላ የተከናወነ ተግባር መኖሩን እንዲረዳ በመንስኤና ውጤት የማስተማር ዘዴ ይዘቶች ተመቻችተዋል ።

ተማሪዎች ንባቡን ደጋግመው ካነበቡ በኀላ በተረዱት ሀሳብ መሰረት በግራፍ መልክ እንዲያሳዩ ሆኗል ። ይኸውም ምን ያህል የምንባቡን መልዕክት ወይም ይዘት እንደተረዱት ለመገምገም ነው።ሌላው የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበው ይዘት ምዕራፍ ስድስት <<በረሀማነት >>( ገፅ 96)ትዕዛዝ አንድ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ በምንባቡ መሰረት እውነት የሆኑትን ትክክል ፣ ውሸት የሆኑትን ስህተት በማለተ መልሱ ።

ሀ. የበረሀማነት አካባቢዎች የአየር ፀባይ ሌሊትና ቀን ተመሳሳይ ነው ።

ለ. የበረሀማ አካባቢ ዝናብ ተከታታይና ከባድ ነው

ምዕራፍ ሰባት፦ ዕርስ << የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ >> (ገፅ107) ለአንብቦ መረዳት

ለ. ማስተማር የቀረቡት ንዑስ ርዕስ <<የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስዔዎች እና ችግሮቹ >> ትዕዛዝ አንድ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ ስጡ።

ሀ.ፀሀፊው ህፃናትን ከምንጋር እንዲነፃፀሩ እና እንዴት እንዳነፃፀራቸው ግለፁ

ለ. የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ በህፃናት ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል ።እነዚህና ሌሎችም ቀርበዋል ።

ከላይ የቀረቡት ይዘቶች አንብቦ መረዳት ለማስተማር ከቀረቡት ምንባቦች ተማሪዎች አካባቢያቸውን ተረድተው ስለ አህጉራቸው ከዚህ ባሻገር ደግሞ ስለ አለም እውቅና እንዲኖራቸው ይዘቶች በጥሩ ሁኔታ በመፅሐፉ ውስጥ ቀርበዋል።

ከዚህም ሌላ ለአንብቦ መረዳት የቀረቡት ይዘቶች መልመጃዎቹ ትዕዛዛቸውን ስንመለከት፡ ትዕዛዝ አንድ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በክፍት ጥያቄ አይነት ቀርበዋል ። ይኸውም ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው በተረዱት መሰረት ሀሳባቸውን እንዲያብራሩ ተደርጓል። ተማሪዎች በማወዳደር እና በማነፃፀር የምንባቡን ሀሳብ የራሳቸውን እወቀት በመጨመር እንዲገልፁ ሆኗል። ይኸውም ተማሪዎችን የሀሳብ አፍላቂነት ለማበረታታት ይጠቅማል ።ከዚህ በማያያዝ በዝግ አይነት የቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት የቀረበላቸውን ምንባብ መሰረት በማድረግ በትክክል የተረዱትን መልዕክት የሚገልፁበት ነው። ይህ የአጠያየቅ አይነት ለተማሪዎች ነፃነት አይሰጥም ። ምክንያቱም እንደክፍት አጠያየቅ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ ጨምረው የሚያብራሩበት ሁኔታ አይኖርም።

በመማሪያ መፅሐፍቱ ምዕራፍ ስምንት ርዕስ ።<< ሰላም >>ላይ ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያነት የቀረቡ ይዘቶችን ለማየት ስንሞክር (ገፅ 22) ትዕዛዝ አንድ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ ።

ለምሳሌ የቀረቡ ፦ ሀ. ሰላም ለእድገት ያለውን አስተዋፆ ግለፁ ።

ለ. የሰላም እጦት በአንድ ሀገር ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ አብራሩ። ሌሎችም ተካተዋል ።ትዕዛዝ ሁለት ፦ የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ በገቡበት አውድ መሠረት ተመሳሳይ ፍች ስጡ ።

ለምሳሌ የቀረቡ ፦ ሀ.ብሒል ለ.አዙሪት ሐ. ከእጅ ወደ አፍ ።እና ሌሎችም በመፀሀፉ ውስጥ ተካተዋል ።

ከዚህ በላይ ለምሳሌ የቀረቡት ጥያቄዎች እና በመፅሀፉ ውስጥ ያሉ ጥያቄዎች ተማሪዎች ከቀረበላቸው ንባብ ለአንብቦ መረዳት ለማስተማሪያነት የቀረቡ ናቸው። የቀረቡት ይዘቶች ተማሪው አንብቦ የተገነዘበውን ሀሳብ ከታሪክ ትምህርቱ ጋር በማያያዝ ማጣቀሻ እያቀረበ እንዲያብራራ በማድረግ ይዘቶች ቀርበዋል። የቀረቡት ይዘቶች ተማሪውን የሚያመራምር እና

የተማሪውን አዕምሮ የሚያጎለብቱ በማድረግ ቀርበዋል። ተማሪዎች የንባቡን ሀሳብ አንብበው በተረዱት መሰረት ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ለመስጠት እንዲችሉ በማድረግ ይዘቶቹ በመፅሀፉ ውስጥ ተካተዋል ። ይኸውም ተማሪው በትክክል አንብቦ ካልተረዳ ለቀረቡት ቃላት ፍች ለመስጠት ያዳግተዋል ።

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ለማስተማር ከቀረቡት ይዘቶች ውስጥ ፦ ምዕራፍ ዘጠኝ ።<< የአየር ንብረት >>አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበው ንዑስ ርዕስ ደግሞ << የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔዎች >> የሆኑትን አብይ ርዕስና ንዑስ ርዕስ ሲቀርቡ ፣

ለምሳሌ ፦ ትእዛዝ አንድ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በንባቡ መሰረት በአጭር ግለፁ ።

ሀ. የአየር ንብረት ለውጥ ምንምን ናቸው ?

ለ. የአየር ንብረት ለውጥ እንዳይከሰት ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ ?

ትዕዛዝ ሁለት ፦ በ"ሀ" ስር የተደረደሩትን ቃላት በ"ለ"ስር ከተደረደሩት ጋር በተመሳሳይ አዛምዱ ።

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ተህዋስ | ሀ. ምክኒያት |
| 2. ተፅዕኖ | ለ. መዛነፌ |
| 3. ሳቢ | ሐ. አበርክቶ |

በመፀሀፉ ውስጥ እነዚህና ሌሎችም ጥያቄዎች ተካተዋል ።

ከላይ የቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎች በሰፊው ሀሳባቸውን ተንትነውና አብራርተው እንዲያቀርቡ በክፍት ጥያቄ ዓይነት የቀረቡ ይኸውም ተማሪዎች ሀሳብ የማመንጨት ችሎታ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። የቀረቡት ይዘቶች፦ አሁን ላይ ለተከሰተ ችግር መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ሀሳብ ለማቅረብ እንዲችሉ የሚያደርግ ይዘት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ችግር እንዳይከሰት ቅድሚያ ጥንቃቄዎች ምንምን ነገሮች መደረግ እንዳለባቸው ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይዘቱ ያስተምራል ። ከዚህ ባሻገር የአንድ ነገር ለውጥ ወይም መቀያየር በህዝቦች ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ በምንባቡ መሰረት ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ይዘቶች ቀርበዋል። በሌላ በኩልም ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት የተዘጋጀውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ቃላትን እንዲያዛምዱ በማድረግ ይዘቱ ቀርቧል።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ለማስተማር በመጨረሻ ላይ የቀረቡ ይዘቶች ፦ ምዕራፍ አስር ዋናርዕስ <<ተውኔት>>አንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበው ንዑስ ርዕስ ደግሞ <<ልጄ -ልጄ-ባይ>>(ገፅ-156) በንባብ ጊዜ በመሀል የቀረቡ ጥያቄዎች

* ባልና ሚስት ከጅምሩ የሚወዛገቡበት በምድነው ?

* ባልን ለችግር ያጋለጠው ምንድ ነው? ተውኔቱ

በምን መልኩ ይጠናቀቃል ብላችሁ ትገምታላችሁ ?ትዕዛዝ አንድ ፦የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት መሰረት መልሱ።

ሀ.ባልና ሚስት የሚወዛገቡበት በምንድ ነው?

ለ. እንደ ቅልብ መጋዣ ደንጋለሳ የሚመቱ ሲል ምን ማለት ነው?

እነዚህና ሌሎችም ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ ተካተዋል። ከዚህ በላይ የቀረቡትን ይዘቶች ከመፅሀፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የተዘጋጁ ናቸው። ተማሪው የቀረበውን ፅሑፍ በሰፊው የሚመረምርበት ሁኔታ አለ። ይኸውም ተማሪው በሚኖረበት ማህበረሰብ ውስጥ ተውኔቱ እደሚያሳየው አንዳንድ ባለ ትዳሮች የሀሳብ አለመግባባት እንደሚኖር ያሳያል የዚህ አለመግባባት መንስዔ ምን እንደሆነ ከአካባቢው ጋር በማያያዝ የሚመራመሩበት ይዘት ነው ።በተውኔቱ ውስጥ እንደታየው የባል ፀባይ ሁኔታ ሲታይ እቢተኛነት የሚታይበት፣ ሰው መክሮት የሰው ምክር የማይቀበል እንደሆነ በቀረበው ገፀ ባህሪ ታይቷል። በተቃራኒው ደግሞ ሚስት በመካሪነት ገፀ ባህሪ የቀረበች ናት። ተው ይህን አታድርግ ፣ ለምን የሰውን ሀሳብ ለመቀበል እንቢተኛ ትሆናለህ ? በማለት የተውኔቱ የሁለቱ ቃለ ምልልስ ያመለክታል ። ይህ ይዘት የቤተሰቦቻቸውን ብሎም የአካባቢያቸውን ሰዎች ፀባይ ከዚህ ምንባብ ጋር በማያያዝ ሀሳባቸውን የሚያገናዝቡበት ይዘት ቀርቧል።

ከዚህ በተጨማሪ የዘመኑ ትውልድ እና የወላጅ የሀሳብ አለመግባባት ለማሳየት ይዘቱ አሳይቷል ። ምሳሌ በፅሐፉ ውስጥ የገፀ ባህሪያት ቃለ ምልልስ (ገፅ 156)" ሹፌር ፦ አባት ይቅርበወት !? እንከባበር ! ባል ፦ ለምን ዝም እላለሁ !? ገና እስከ ክርህ እነግርሀለሁ ። ለመሆኑ እናንት የዘመኑ ልጆች እግዜር የሰጣችሁን እድሜ በወጉ ብትጨርሱት ምናለበት ! ለምን ወደ ሞት ትቸኩላላችሁ? ለዚህ እኮ ነው በዚህ ዘመን አባቴ አባቴ ብላችሁ ማልቀሳችሁ ቀርቶ እናንተ ቀድማችሁ እኛ ቆመን ልጄ- ልጄ -ብለን የምናለቅሰው።

ሹፌር፦ አሃ----አሁን ገባኝ ልጄ -ልጄ ብሎ ማልቀስ ስለቀፍፍዎት ቀድመውን ሲሞቱ ተክለፍልፈው ከመኪና መንጋ መካከል የገቡት ? "በመማርያ መፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረበው ቅንጫቢ ተውኔት ይዘት እንዲሚያመለክተው ወጣቱ ትውልድ ወላጆቹ የሚሰጡትን ገንቢ ሀሳብ በአዎንታዊ መልክ እንደማይቀበለው ያሳያል ። ይልቁንም ወላጅ ለሰጣቸው ገንቢ አስተያየት ከመቀበል ይልቅ ተቃራኒ ሀሳብ የሚሰጡ መሆኑን በማሳየት ይዘቱ አስተማሪ በመሆን ቀርቧል። ከዚያም ሌላ በቀረበው የአንቡቦ መረዳት ንባብ ሀሳቡን በመረዳት ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍች እንድሰጡ በመሆን የቀረበ ነው ።በመሆኑም ተማሪውን አንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር ያግዘዋል።

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ የተማሪው መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ምንባቦች የቋንቋ ግልጽነት እና የሀሳብ አሻሚነት ሁኔታ እንዴት አያችሁት?

**ተጠያቂ መምህር 1 የሰጡት መልስ**

ለአንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች የቋንቋ ግልጽነት አላቸው የሀሳብ አሻሚነት የላቸውም ለተማሪዎች በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ በመሆኑ የመረዳት ችግር የለባቸውም ነገር ግን ምንባቦቹ አርትኦት የጎደላቸው ናቸው።

**ተጠያቂ መምህር 2 የሰጡት መልስ**

ለአንብቦ መረዳት እና ፅሕፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች በጥሩ ሁኔታ የቀረቡ አይደሉም። ምንባቦች ተያያዥ የላቸውም። ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ እንዲሰለች ያደረገ ነው። አንዱ ይዘት እያለ ሌላ ይዘት የሚቀርብበት ሁኔታ ይታያል።

**ተጠያቂ መምህር 3 የሰጡት መልስ**

ምንባቡ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ነው። የሀሳብ ግልፅነት አላቸው አንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች የሀሳብ አሻሚነት የላቸውም ግልጽነት አላቸው።

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህር 4ኛው መልስ**

ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች በአብዛኛው ግልጽነት አላቸው። ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን የሀሳብ አሻሚነት አለበት፣ ይዘቶች ተደጋግመው ይቀርባሉ።

5ኛ ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት መልስ

ክሂሎቹን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ኤዲቲንግ አለባቸው የሀሳብ መደራረት አለባቸው፡፡

ከላይ ለመምህራን ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ምላሽ ለማየት እንደተሞከረው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች የቋንቋ ግልጽነት እና የሀሳብ አሻሚነት እንዳላቸው ሶስቱ መምህራን ሲገልፁ ፥ሁለቱ መምህራን ደግሞ የሀሳብ ግልጽነት ያላቸው መሆኑን መልሳቸውን ሰጥተዋል ፡፡ከቃለ መጠይቁ መረዳት እንደተቻለው መፅሀፉ የሀሳብ ግልጽነት ውስንነት እና የሀሳብ አሻሚነት እንዳለው ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል ፡፡

## 4.6. በመፅሐፉ ውስጥ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች

ለአንድ ነገር ክህሎት መዳበር ቀደም የሚደረግ ልምምድ ውጤት ነው፡፡ የመፃፍ ችሎታችን የሚዳብረው ቀድመን በተለያዩ ደራሲያን የተፃፉ ፅሑፎችን ማንበብ ስንችል ነው፡፡ ስለ ፅህፈት ይዘቶች አቀራረብ ታደሰ ሲባም (ዶ/ር) 2007 PGDT ትምህርት ለማስተማሪያ በዘጋጁት ሞጁል እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> " የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በሁለት ክፍሎች ተከፍለው የሚታዩ ናቸው ፣ *ውጤታዊ እና ሂደታዊ አቀራረብ ፡፡* ውጤታዊ አቀራረብ ፦ ዋነኛ ትኩረቱ ተማሪዎች በፅህፈት ተግባራቸው መጨረሻ ላይ በሚያገኙት ውጤት ቅርፅ ላይ እንጅ ከጽህፈቱ ሂደት ውስጥ በማለፋቸው ብቻ አይደለም፡፡
>
> የዚህ አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች የተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶች እንዲጠቀሙና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች እና የአንቀጽ ክፍሎችን ቅንብር እንዲካኑ ያስችላቸዋል፡፡
>
> * ሂደታዊ አቀራረብ ፦ ሂደታዊ አቀራረብ ቃሉ እንደሚያስከትለው ዋነኛ ትኩረት በመጨረሻው ወይም በውጤቱ ለይ ሳይሆን አሰራር ሂደቱ ላይ ነው፡፡ ለሂደታዊ አቀራረብ መከሰትምክንያት የሆነው በተለይ በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ የተነሱት የሂደት ተኮር አራማጆች በውጤት ተኮር የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ላይ ጉልህ የሆነ ድክመት እንዳለበት በመግለፃቸውና በማመልከታቸው ነው፡፡ "

ከላይ ታደሰ(ዶ/ር) እንደገለፁት ሁለት አይነት የፅህፈት ትምህርት አቀራረቦች እንዳሉ ገልፀዋል ።በውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች የተለያዩ አፃፃፍ ዘዴ እንዲጠቀሙ ፣ ዓረፍተ ነገሮች እና አንቀፆችን በስርዓት አቀነባብረው እንዲፅፉ ያግዛል። ሁለተኛው የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ሂደታዊ አቀራረብ የፅህፈት ትምህርት የአሰራር መንገዱን የሚያመለክት አቀራረብ ነው። ይኸውም ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚያፈልቁ ፣ የፅሑፍ ረቂቃቸውን መላልሰው የሚመለከቱበት ፣ በመጨረሻም ስህተታቸውን በማረም የተሻለ ፅሑፍ እንዲፅፉ የሚያሳይ አቀራረብ ሂደት ነው።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ስንመለከት ፦ ምዕራፍ ሁለት ፦ <<ባህላዊ ቅርሶች >>(ገፅ 32) ትዕዛዝ ሁለት ፦ ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ ከሁለት አንቀጽ በላይ አመዛዛኝ ድርሰት ፃፉ።

ለምሳሌ፦ ሀ. ቴክኖሎጅ እና ተማሪ

ለ. ክፋትና ደግነት

ሐ. ዕውቀትና ገንዘብ (ገፅ 34)

አንደኛ ትዕዛዝ ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ ተገቢ የሆነ መልስ ስጡ። የሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዩች ከሶስት አንቀፅ በላይ አመዛዛኝ ድርሰት ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡ ። ምዕራፍ አራት << አጭር ልቦለድ >> (ገፅ 67) ትዕዛዝ አንድ ፦ ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተዘረዘሩትን አረፍተነገሮች አያይዙ

ሀ. ሰላም የሚገኘው ተቻችሎ በመኖር ነው።

ለ. ሰላም የሚገኘው ተከባብሮ በመኖር ነው ።

ሐ. ሰላምየሚገኘው የጋራ ፍላጎት ሲኖር ነው ።

ምዕራፍ አምስት ርዕስ<<ህዝብ >> ( ገፅ 80) ትዕዛዝ አራት ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መንስኤና ውጤት ለይታችሁ ፃፉ ። ሀ. በአካባቢያችን የጣለው ዝናብ ከባድ ጎርፍ መጥለቅለቅ አስከተለ። መንስኤ ----ውጤት እነዚህንና ሌሎች መሠል ይዘቶች መፅሐፉ ውስጥ ተካተዋል።

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ይዘቶች ተማሪው ሁለት ነገሮችን በማነፃፀር እና በማወዳደር ድርሰት እንዲፅፉ የቀረበ ይዘት ነው ።ተማሪው ሁለት ነገሮችን ሲያነፃፅር ትኩረት ሊያርግባቸው የሚገባ ሀሳቦች እውቀና ሊኖረው ይገባል። ሁለት

ነገሮችንበሚያወዳድሩበትጊዜስለ ሁለቱ የሚወዳደሩ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ሲያወ ዳደሩ አእምሮው ብዙ ሀሳቦችን እንዲመራመሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለ ጉዳዮች ጥቅምና ጉዳት ፣ጠንካራና ደካማጎን ፣ ሊሰጡ የሚችሉትን ጠቀሜታ ... የመሳሰሉትን ሀሳቦች በውል ሊያጤኑ ይገባቸዋል ፡፡ ተማሪዎች ስለ ሁለቱ ጉዳዮች አነፃፅረው አንቀፅ በሚፅፉበት ወቅት የቃላት ምርጫ ፣ የሀሳብ ቅደም ተከተል የዓ/ነገሮች አገባብ በስርዓት ማጤን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ለፅህፈት መዳበር ፋይዳ ያላቸው ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች አንዱን ሐሳብ ከሌላው ሀሳብ ጋር በአያያዝ ቃላት በማቀናጀት ፅህፈትን እንዲለማመዱ ተደርጎ ቀርቧል

ከዚህ በተጨማሪ በይዘቶቹ ውስጥ እንደተገለፀው ተማረዎች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ሀሳቦችን እያቀናጁ እንዲፅፉ በማድረግ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በይዘትነት ቀርቧል ፡፡

ከዚህ ባሻገር ደግሞ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የተከሰተውን አጋጣሚ ሁኔታ በትኩረት በመመልከት እና በመመራመር የጉዳዩንመነሻ አስመልክተው ሰፊ ማብራሪያ በፅሑፍ እንዲሰጡ በማድረግ ፅህፈትን ለማስተማር በመንስዔና ውጤት ቀርቧል፡፡

## 4.7 በመፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳትና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ትንተና

ምዕራፍ ሁለት ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የቋንቋ ክሂሎች የምንላቸው ማዳመጥ ፣ መናገር ፣ መፃፍ እና ማንበብ ሲሆኑ ፣ እነዚህ ክሂሎች የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም አንዱን ክሂል ብቻ ለማስተማር የማይቻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ማዳመጥ ለማስተማር ንግግር መኖር አለበት ፣ ማንበብክሂል ለማስተማር የተፃፈ ፅሁፍ መኖር አለበት፡፡ ስለዚህ አንዱን ክሂል ስናስተምር አንዱ ሊኖር ይችላል ማለት ነው ፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች፦ ምዕራፍ ሁለት <<ባህላዊ ቅርሶች >> (ገፅ 32) ሐ. ከመፅሐፍ በማንበብ አምስት ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመፃፍ ስለ አጠቃቀማቸው ከክፍል ጎደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ ፡፡ ምዕራፍ ሶስት << ሰብዊ እሴቶች >> (ገፅ 49) ትዕዛዝ ሁለት ፦ ቀጥሎ የቀረበውን ንባብ አንብባችሁ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ጥምር ቃላት ለይታችሁ አውጡ፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡትን አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎችን የሚያመራምሩ ናቸው ፡፡

ተማሪዎቹ  የቀረበላቸውን ንባብ ሀሳባቸውን በመሠብሰብ ለሚነበበው ንባብ ትኩረት በመስጠት በነቃ ህሌና ንባቡን ያነባሉ ። ከዚያም  በኋላ የንባቡንአጠቃላይ መልዕክት ወይም ደራሲው ሊያስ ተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ መረዳት ይጠበቃል ። በተጨማሪም የተረዱትን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ፅሀፈት አንድፅፉ የተደረገበት ሁኔታ አለ።

 ተማሪዎች የተረዱትን ሀሳብ ሲፅፉ ምንባቡ  ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ ሳያዛቡ እና የራሳቸውን ሀሳብ በማመንጨት ፅሀፈትን  እንዲለማመዱ ይዘቶቹ  ተካተዎል።

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና ፅሀፈትን ለማስተማር በማቀናጀት ለማስተማር የቀረበው የሌላው ይዘት ደግሞ ፦

ምዕራፍ አራት ፦ << አጭር ልቦለድ >> (ገፅ 63) ላይ ትዕዛዝ ሶስት ፦ ንባቡን ደጋግማችሁ በማንበብ በውስጡ ያሉ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በመለየት ፍቻቸውን ግለፁ ። ምዕራፍ አምስት ፦ << ህዝብ >> (ገፅ 80) ላይ ትዕዛዝ ሶስት ንባብ ደጋግማችሁ በማንበብ የክልላችን ህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያሳይ ግራፍ ስሩ። ( ገፅ 82) ትዕዛዝ አንድ ፦ ከዚህ በታች ለተራኪ ድርሰት በምሳሌነት የቀረበ ስለሆነ በጥሞና አንብባችሁ  የታሪክ ቅደም ተከተሉን ፅፉችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ። እነዚህ እና መሠል ይዘቶች በመፅሃፉ ውስጥ ተካተዋል ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ይዘቶች በመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ፣ ይዘቶቹ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በፅሁፍ እንዲገልፁ  የሚያደርጉ ናቸው ።ይኸውም ተማሪዎች ንባቡን በተደጋጋሚ ማንበብ እንዳለባቸው እና የንባቡን ሀሳብ እንዲረዱ ይገልጻል ።

ከዚያ በኋላ በምንባቡ ውስጥ ለሚገኝ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች እንድሰጡ ይጠቁማል ። በዚህን ጊዜ ተማሪዎች በአእምሮቸው አከማችተው ያስቀመጡትን ሀሳብ ወይም አንብበው የተረዱትን መሰረት በማድረግ በፅሑፍ ፍች ይሰጣሉ ። ይህ ይዘት አንብቦ መረዳት እና ፅሀፈትን በውህደት አቅርቧል ለማለት ያስችላል።

በሌላ በኩል ተማሪዎች ንባቡን በማንበብ የተረዱትን ሀሳብ ወይም በምንባቡ ውስጥ ያገኙትን የህዝብ ቁጥር በግራፍ እንዲያሰፍሩ ( እንዲያሳዩ )በማድረግ ቀርቧል ። ተማሪው አንብቦ የተረዳውን ሀሳብ በግራፉ ሲያሳይ አእምሮውን እየመረመረ ሀሳቡን በግራፍ የሚገልፅበት ሁኔታ ቀርቧል ።

ከዚህ በተጨማሪ ለአንብቦ መረዳት እና የፅሀፈትን ክሂል በጥምረት ለማቅረብ የተዘጋጀውን ንባብ (ድርሰት) አንብበው የንባቡን ሀሳብ ቅደም ተከተል አብራርተው የሚፅፉበት

ሁኔታ ይጠቆማል በስርዓት ፅፈው አቀነባብረው ለመምህራቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ ክሂሎቹን እንዲማሩ ተደርጓል።

አንድን ንባብ ካነበቡ በኋላ የታሪክ ቅደም ተከተሉን በማስቀመጥ በፅህፈት ለማቅረብ ሲሞከር ፣ አንባቢው ለንባቡ ትኩረት ሠጥቶ ማንበብ ይጠይቃል ። ያለዚያ ግንየንባቡን ቅደም ተከተል ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ይሆናል ።

በመጨረሻም በፅሐፉውስጥ አንብቦ መረዳትአና ፅህፈትን በቅንጅት ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ፦ ምዕራፍ ሰባት <<የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ>> ( ገፅ 109) ትዕዛዝ ሶስት ፦ ንባቡን ደጋግማችሁ በማንበብ በምንባቡ ውስጥ ያሉ ፈሊጣዊ ንግግሮችን በመለየት አውዳዊ ፈቻቸው ግለፁ። ለምሳሌ ያህል፦ ዳር የለለው ( ገደ ብ የለሽ)( ገፅ 110) ትዕዛዝ አምስት ፦ ከዚህ በታች የቀረበውን ንባብ አንብባችሁ በውስጡ የሚገኙ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ለይታችሁ ፃፉ።(ገፅ111) ትዕዛዝ ሁለት፦ ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዩች መፅሀፍ በማንበብና የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ በማሰባሰብ አጠናቅራችሁ ድርሰት ፃፉ ።

ለምሳሌ፦ ሀ.የፃታ እኩልነት

ለ. የሀይማኖት እኩልነት

ሐ . የዜጎች እኩልነት

እነዚህ እና ሌሎችም ይዘቶች በመፅሐፉ ውስጥ ተካተዋል።

ከዚህ በላይ የተገለፁት ይዘቶች በመፅሐፉውስጥ የሚገኙ ናቸው። አንብቦ መረዳትና ፅህፈትን በጥምረት ለማስተማር ተማሪዎች ንባቡን ደጋግመው እንዲያነቡ ይመክራል ።

ከዚያ በኋላ የተረዱትን ሀሳብ መሠረት በማድረግ መልመጃዎችን በአውዱ መሠረት ፍች እንዲሰጡ በማድረግ ቀርቧል ።

ሌለኛው ይዘት ደግሞ ተማረዎች በመፅሀፉ ውስጥ የቀረበላቸውን ንባብ በማንበብ እና መረጃ ይኖራቸዋል ብለው የገመቷቸውን ሰዎች በመጠየቅ መረጃዎችን ማከማቸት (መሰብሰብ) እንዳለባቸው ይገልፃል። ከምንባቡ እና ሰዎችን ጠይቀው ያገኙትን መረጃ አጠናቅረው በቀረበላቸው ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ድርሰት እንዲፅፉ

በማድረግ ይዘቶች ቀርበዋል።

**በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና ለፅህፈት ክሂል ትኩረት የመስጠት ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**ተጠያቂ መምህር 1ኛው የሰጡት መልስ**

መጽሐፉ ሲዘጋጅ ለአንብቦ መረዳት እና ለጽሕፈት ክሂል አቀናጅቶ የማቅረብ ሁኔታ ሲታይ ትኩረት ተሰቶ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይዘቶች በሰፊው ቀርበዋል፡፡

**ተጠያቂ መምህር 2ኛው የሰጡት መልስ**

የ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ለሁለቱ ክሂሎች ትኩረት በመስጠት ተዘጋጅቷል፡፡ ተማሪዎችን አሳታፊ ነው፡፡

**ተጠያቂ መምህር 3ኛው የሰጡት መልስ**

በአብዛኛው መጽሐፉ ለአንብቦ መረዳት ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ ለአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የይዘቶች አቀራረብ ውስንነት ይታይበታል፡፡

**ተጠያቂ መምህር 4ኛው የሰጡት መልስ**

በአብዛኛው መጽሐፉ ለአንብቦ መረዳት ትኩረት የሰጠነው፡፡ ለአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የይዘቶች አቀራረብ ውስንነት ይታይበታል፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 5ኛው መልስ**

በ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ ይዘቶች ውስን ናቸው፡፡ እንደ ማዳመጥ፣ አንብቦ መረዳት፣ መናገር እና መፃፍ ሁለቱን ክሂሎ አቀናጅቶ ከማቅረብ አኳያ ብዙም ትኩረት አልተሰጠውም፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 6ኛው መልስ**

ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ ሰፋ አድርጎ የሚያቀርበው የፅሕፈት ክሂል እና የአንብቦ መረዳትን ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱን ክሂሎች አዋህዶ የማቅረብ ሁኔታ ሲታይ ውስን ነው፡፡

በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ትኩረት የመስጠት ሁኔታ ሲታይ በአብዛኛው መምህራን ውስንነት የሚታይበት መሆኑን መልሳቸውን ሲሰጡ ሁለት መምህራን ደግሞ መጽሀፉ ትኩረት በመስጠት የተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል ። በመሆኑምከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው ትኩረት ተሰጥቶ ቢዘጋጅም ውስንነት እንዳለበት ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመላክታል ።

## 4.8 አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል የቀረቡት/የተዘጋጁት/ ምንባቦች ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋ ግልፅነት ሁኔታ

በ2015 ዓ.ም ለማስተማሪያነት ተግባር ላይ የዋለው የ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር በርካታ ምንባቦች ቀርበዋል። የተዘጋጁበት የቋንቋ ሁኔታ ሲታይ በአብዛሃኛው ግልፅነት ያላቸው፣ሁሉም ተማሪዎች በሚረዱበት ሁኔታ ቀርበዋል ። ቢሆንም በዚህ ጥናት አልፎ አልፎ እንደ ታየው የተወሰኑ ግልፅነት የሌላቸው ቃላቶችም ይገኛሉ። ይኸውም ተማሪዎች አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አዋህዶ ለመማር እንከን የሚፈጥሩበት ሁኔታ ይኖራል።

በመፅሐፉ ውስጥ ግልፅነት የሌላቸው ቃላት ለምሳሌ ያህል ሲቀርቡ ፡-ምዕራፍ ሁለት ፡-ገጽ 27 ተለምዶዎ፣ የሚንቁሱና፣ ምዕራፍ ሶስት ፡-ገጽ 45 ሽክማቸውን ፣ተውስኖባቸው፣ምዕራፍ ስድስት ፡- ገበሎ፣ ምዕራፍ ሰባት፡-ገጽ 107 አታወቅም፣ ብለፅግና ምዕራፍ አስር፡- የሚበቅቱኝ፣ የሚፈትሩኝ፣ ያምቧልልዎት፣ ሽረዎት፣ ስሽናክል፣ ጭዳ፣ የሚቧርቁት፣ እንዷን፣ የግዜ ልዩነበት የመሳሰሉት ቃላት ቋንቋቸው በጣም ግራ አጋቢ በመሆኑ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አዋህዶ ለመማር ምቹነት የሌላቸው ናቸው።

## 4.9. አንብቦ መረዳት እና ፅህፍትን አቀናጅቶ ለማስተማር የመምህሩ መምሪያ አቀራረብ ሁኔታ

የመምህሩ መምሪያ መፅሐፍ አገልግሎቱ ወይም ፋይዳው መምህሩ የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ እንዴት አድርጎ እንደሚያስተምር አቅጣጫ የሚያሳይ መሳሪያ ነው ። በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት የራሱን ዕውቀት በመጨመር የመማር ማስተማሩን ስራ ያከናውናል።

"የመምህሩ መምሪያ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መረሃ ትመህርቱን መሠረት በማድረግ ነው። በመፅሐፉ እያንዳዱ ምዕራፍ የሚሸፈንበትን የክፍለ ጊዜ ብዛት አስቀምጧል ።"

ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመምህሩ መምሪያ በመርሃ ትምህርቱ መሠረት የተዘጋጀ ነው፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ ስንት ክፍለ ጊዜ እንደሚወስድ ይገልፃል፡፡ ይህንንም ከዚህ በታች በሰንጠረዥ እንመለከታለን ፡፡

ሰንጠረዥ አራት፡-በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተማሪው መፅሐፍ ያሉ ምዕራፎች ስንት ክፍለ ጊዜ እንዳለባቸው የሚታይ ሰንጠረዥ፡-

| ተ.ቁ | ምዕራፎች | የምዕራፎች ዋና ዋና ርዕሶች | የክፍለ ጊዜ ብዛት | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምዕራፍ አንድ | ስራና የስራ ስነ ምግባር | 9 ክፍለ ጊዜ | 9.6 % |
| 2 | ምዕራፍ ሁለት | ባህላዊ ቅርሶች | 12 ክፍለ ጊዜ | 12.9 % |
| 3 | ምዕራፍ ሦሥት | ሰብዓዊ ዕሴቶች | 12 ክፍለ ጊዜ | 12.9 % |
| 4 | ምዕራፍ አራት | አጭር ልቦለድ | 12 ክፍለ ጊዜ | 12.9 % |
| 5 | ምዕራፍ አምስት | ህዝብ | 9 ክፍለ ጊዜ | 9.6 % |
| 6 | ምዕራፍ ስድስት | በረሃማነት | - | - |
| 7 | ምዕራፍ ሰባት | የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ | 9 ክፍለ ጊዜ | 9.6 % |
| 8 | ምዕራፍ ስምንት | ሠላም | 9 ክፍለ ጊዜ | 9.6 % |
| 9 | ምዕራፍ ዘጠኝ | የአየር ንብረት | 9 ክፍለ ጊዜ | 9.6 % |
| 10 | ምዕራፍ አስር | ተውኔት | 12 ክፍለ ጊዜ | 12.9 % |
| ጠቅላ | አስር ምዕራፍ | አስር ርዕሶች | 93 ክፍለ ጊዜ | 100 % |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደታየው ምዕራፍ 2፣3፣4እና 10 48 ክፍል ጊዜ ወይም በፐርሰንት 61% ሲኖራቸው፣ምዕራፍ 1 ፣5፣7፣8 እና 9 ያላቸው ክፍለ ጊዜ ብዛት 45/48.3 ሲሆን፣ከዚህ በተለየ ምዕራፍ ስ ድስት‹‹በረሃማነት›› የሚለው ርዕስ ስንት ክፍለ ጊዜ እንደተሰጠው ከመምህሩ መምሪያ መፅሐፍ የተገለፀ የክፍለ ጊዜ መጠን የለም፡፡

## 4.10. በመምህሩ መምሪያ መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አዋህዶ ለማስተማር አቅጣጫ የማሳየት ሁኔታ

የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማ የመምህሩ መምሪያ የመሪነት ሚና ይጫዎታል፡፡ በመሆኑም በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ ሁለቱን ክሂሎች አዋህዶ ለማስተማር የሚቻልበትን ሁኔታ ከመምህሩ መምሪያ ለምሳሌ ያህል እንደሚከተለው

ቀርቧል፡፡ "በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ማዳበር ነው፡፡ ስለሆነም እስካሁን ያነበቧቸውን ፅሑፌ ተውኔቶች በአብነት በመጠቀም በሚመችዎ መልኩ ተውኔት እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡በፃፉት ተውኔት ላይም በተማሩት ትምህርት መሠረት በቡድን ተወያይተው ማስተካከል ያለባቸውን እንዲያስተካክሉ ካደረጉ በኋላ ጽሁፋቸውን ተመልክተው የዕርምት ግብረ መልስ ሰጥተው ትምህርቱን ያጠናቁ (የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የመምህሩ መምሪያ) ከላይ ለማሳየት የቀረበው ሃሣብ ተማሪዎች ፅሑፌ ተውኔቱን አንብበው ከተረዱ በኋላ በዚያ መሠረት ተውኔት እንድፅፉ መምህሩን ይመራል ፡፡ ከዚያ በኋላ በፃፉት ፅሑፍ ላይ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ በማለት ይገልፃል ፡፡ ይኸውም ከመምህሩ መምሪያ ሀሳብ እንደተገለፀው አንብቦ መረዳት፣ ፅህፈት እና የንግግር ክሂል ተቀናጅተው መቅረባቸውን ለማሳያ ያህል የቀረበው ፅሑፍ ይገልፃል ፡፡

በ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማቅረብ በመማር ማስተማሩ ምን ምን ዘዴዎች ትጠቀማላችሁ?

**ተጠያቂ መምህር 1ኛው የሰጡት መልስ**

በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማቅረብ የምንጠቀማቸው ዘዴዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በኋላ የምንባቡን ሀሳብ ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁለቱን ክሂሎች በማቀናጀት ለማስተማር እንሞክራለን፡፡

**ተጠያቂ መምህር 2ኛው የሰጡት መልስ**

በመጽሐፉ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አቀናጅተን ለማስተማር የምንጠቀመው ዘዴ፣ ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ እንዲጽፉ እናደርጋለን፣ ከምንባቡ ውስጥ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ሰጥተው እንዲጽፉ እናበረታታለን፡፡

**ተጠያቂ መምህር 3ኛው የሰጡት መልስ**

የጽሕፈት እና የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማስተማር የምንጠቀምበት ብልሀት ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የተረዱትን ሀሳብ በጽሑፍ አንድ ግልጽ እናደርጋለን፡፡ ከምንባቡ ለወጡ መልመጃዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ እናደርጋለን፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 4ኛው መልስ**

ሁለቱን ክሂሎች አዋሀዶ ለማስተማር የምንጠቀማቸው ዘዴዎች በመጽሐፉ ውስጥ መልመጃዎችን ለመስራት በቀረቡት ትዕዛዞች መሠረት ተማሪዎቹ እንዲሳተፉ እናደርጋለን፡፡ ለምሳሌ፡- ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ተማሪዎች ከፃፉ በኋላ የማንበብ ክሂላቸው እንዲዳብር የፃፉትን እንዲያነቡ እናደርጋለን፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 5ኛው መልስ**

በመጽሐፉ ውስጥ ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅተን ለማስተማር የምንጠቀመው ስልት ተማሪዎች ከራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ የፃፉትን ሀሳብ ደጋግመው እንዲያነቡ እናደርጋለን በዚህ ዘዴ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል አቀናጅተን እናስተምራለን፡፡

ከላይ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ መልስ መረጃ እንደተገኘው በመፅሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማቅረብ መምህራን የሚጠቀሟቸው ዘዴዎች ምንባቡን ተማሪዎች ካነበቡ በኋላ የምንባቡን ሀሳብ ጠቅለል አድርገው እንድፅፉ በማድረግ እንደሚያስተምሩ መምህራን ሀሳባቸውን ሰጥተዋል ፡፡

## 4.11. የተማሪ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አዋሀዶ መልመጃዎችን የማቅረብ ሁኔታ

8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተማሪ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አዋሀዶ ለማቅረብ መልመጃዎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ሁኔታና የአንብቦ መረዳት እና የፅሕፈት ክሂል ቅንጅት በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ መምህራን እንደሚከተለው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል

በ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል አዋህዶ ለማቅረብ መልመጃዎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ሁኔታ ምን ይመስላል?

**ተጠያቂ መምህር 1ኛው የሰጡት መልስ**

የመልመጃዎች ሁኔታ ሲታይ መጽሀፉ ሁለቱን ክሂሎች አዋህዶ ያቀረበ ነው፡፡ ተማሪዎችን በሚመዝን ሁኔታ የቀረበ ነው፡፡ ለመልመጃዎች ትኩረት በመስጠት የተዘጋጀ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች አካባቢያዊ ጋር የተዛመደ ወይም ያቀረቡት ምንባቦች አካባቢውን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ችግር ብዙም አይገጥማቸውም፡፡ ስለዚህ የተረዱትን ሀሳብ ደግሞ በጽሑፍ አብራርተው ይገልፃሉ፡፡ የመልመጃዎች ለመስራት የቀረቡት ትዕዛዞች ሁኔታ ሲታይ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጁ እና ከጥያቄዎች ጋር ተያያዥ ያላቸው ናቸው፡፡ ጥያቄዎችን ለመስራት ግራ የሚያጋቡ ናቸው፡፡

**ተጠያቂ መምህር 2ኛው የሰጡት መልስ**

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ከአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ጋር መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከአካባቢው ጋር ግንኙነት ያላቸው ምንባበች ተዘጋጅተዋል፡፡ በ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የትዕዛዞች ግልጽነት ሲታይ ትዕዛዞች በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ተማሪው ጥያቄዎችን ለመስራት የሚያነሳሱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የአርትኦት ክፍተት

**ተጠያቂ መምህር 3ኛው የሰጡት መልስ**

የ8ኛ ክፍል የተማሪው አማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍ ከተማሪው ህይወት ጋር ወይም አካባቢውን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ ከተማሪው ጋር የተዘጋጁት ይዘቶች የግንኙነት ውስንነት አለባቸው፡፡ ሁለቱን ክሂሎች ለማስተማር የትዕዛዞች ሁኔታ የተንዛዛ ነው፡፡ ትዕዛዞች አንብቦ ለመረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ ግልጽነት የላቸውም የትዕዛዞች አወዛጋቢነት ይታይበታል መጽሐፉ፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 4ኛው መልስ**

የሚቀርቡት ምንባቦች በአብዛኛው አካባቢን መሠረት ያላደረጉ ናቸው፡፡ ተማሪው ህይወት ጋር ብዙም ግንኙነት የላቸውም፡፡ መልመጃዎችን ለመስራት የትዕዛዞች ሁኔታ ብዙም ግልፅ አይደለም፡፡ በምን ሁኔታ መልመጃዎች እንደሚመለሱ አያብራሩም፡፡

**ቃለ መጠይቅ የተደረገላት መምህርት 5ኛው መልስ**

በ8ኛ አማርኛ ቋንቋ ማስተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች አካባቢያዊ ናቸው፡፡ የአካባቢውን መስህብ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ከተማሪው ህይወት ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር መልመጃዎችን ለመስራት የቀረቡት ትዕዛዞች አንዳንዶች ግራ የሚያጋቡ ናቸው፡፡ መልመጃዎችን በምን ሁኔታ እንደሚሰሩ አያብራሩም፡፡ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ሁለቱን ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የመልመጃዎ አቀራረብ ሲታይ በጥሩ ሁኔታ እንደዘጋጁ ሁሉም መምህራን ለቃለ መጠይቁ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል ፡፡ምንባቦቹን ከተማሪዎች ህይወት ወይም አካባቢውን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ መሆኑን ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያስረዳል ፡፡ሌላው የአንቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂልን ለማስተማር መልመጃዎችን ለመስራት የትዕዛዞች ሁኔታ ሲታይ ግልጽነት የሌላቸው እና የተንዛዛ ሀሳብ የሚያቀርቡ መሆኑን በአራት መምህራን ቃለ መጠይቅ መረጃ የተሰጠ ሲሆን አንድ መምህር ደግሞ መልመጃዎችን ለመስራት ትዕዛዞች ግልጽነት አላቸው በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል ፡፡በመሆኑም በመፅሀፉ ውስጥ መልመጃዎችን ለመስራት ትዕዛዞች ውስንነት እንዳላቸው ከቃለ መጠይቁ የተገኙው መረጃ ያመለክታል ፡፡

# ምዕራፍ አምስት:-ማጠቃለያ፣የጥናቱ ግኝት እና የመፍትሄ ሃሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ በ2015 ዓ/ም አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መፅሐፍ ለ8ኛ ክፍል ባዘጋጀው መፅሐፍ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና የዚህ ጥናት ትኩረት ነው፡፡

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት መፅሀፉ የመፃፍ ክሂል እና የአንብቦ መረዳት ክሂል አቀናጅቶ ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቅርቧል? የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋ ግልፅነት መኖር እና አለመኖሩን ለማየት እና በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት መረጃዎች ግልፅነት ምን ይመስላል?የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመርመር ነው ፡፡የጥናቱ አላማ በተማሪው መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና መልመጃዎች መመርመርና መተንተን ፥ሁለቱን ክሂሎ ለማስተማር የቀረቡትን ምንባቦች ግልፅነት ማየት እና መልመጃዎችን ለመስራት የትዕዛዞች ግልፅነት መመርመር ነው ፡፡የጥናቱ ዘዴ በተመለከተ ለዚህ ጥንታዊ ፅሁፍ የአጠናን ዘዴ ተግባር ላይ የዋለው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ እና በደጋፊነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል ፡፡የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ እና በ2015 ዓ.ም የታተመውን መፅሀፍ የሚያስተምሩ መምህራን ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመሆን ግልጋሎት ላይ ውለዋል ፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተመለከተ የሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ መረጃዎችን ለማግኘት ጥቅም ላይ ውለዋል ፡፡

## 5.2 የጥናቱ ግኝት

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ዓላማ በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ችሎታን አዋህዶ መቅረባቸውንና አለመቅረባቸውን መመርመር ነው፡፡ ይህ ጥናት ለማየት እንደሞከረው አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር ይዘቶች እና መልመጃዎች ተካተዋል፡፡ ቢሆንም ከብዛት አንፃር ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ከማቅረብ አኳያ ውስንነት አለበት፡፡

የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት (የተዘጋጁት) ምንባቦች ክሂሉን ለማዳበር ቋንቋ ግልፅነት ሁኔታ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የትንተና ውጤት እንደሚያሳየው ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች የቋንቋ ሁኔታ ሲታይ በአብዛሃኛው ተማሪዎች የሚረዷቸው ተደርገው ቀርበዋል ፡፡ ቢሆንም በጥናቱ እንደተፈተሸው ግልፅነት የሌላቸው ቃላትም ወይም ቋንቋቸው ግልፅ ያልሆኑ ለመረዳት የሚያስቸግሩም ተገኝተዋል ፡፡

የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ በ 8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ትዕዛዝ ግልፅነት መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ትዕዛዝ በጥናቱ ትንተና እንደታየው በጥሩ ሁኔታ የቀረቡ ናቸው፡፡ ነገር ግን አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የትዕዛዝ ሁኔታ ሲታይ ፣በቃል እንዲመለሱ የተደረጉ 2፣መልመጃዎቹ በፅሑፍ እንዲመለሱ የሚገልፁ ትዕዛዞች ብዛት በቁጥር 16፣መልመጃዎቹ በፅሑፍ ወይም በቃል እንዲመለሱ ግልፅነት የሌላቸው ትዕዛዞች ብዛት በቁጥር 15፣በጠቅላላው አንብቦ መረዳት ለማስተማር ለቀረቡ መልመጃዎች ትዕዛዝ ብዛት 33 ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሐሳብ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መልስ ለመስጠት የትዕዛዞች ግልፅነት አለመኖር ተማሪዎችን ግራ የማጋባት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሐሳብ

በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ በምርምር ያገኛቸውን ውጤቶች መሠረት በማድረግ ጥናት አድራጊው እንደሚከተለው የመፍትሔ ሀሳቦችን አስቀምጧል ፡፡

- ❖ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል አቀናጅቶ ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቅርቧል፡፡ ቢሆንም ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ ውስንነት ይታይበታል፡፡ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በፅሑፍ ለመግለፅ ይዘቶች እና መልመጃዎች በሰፊው ቢዘጋጁ ለተማሪው ክህሎት መዳበር አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡
- ❖ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂል በቅንጅት ለማስተማር በርካታ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ የቋንቋ ግልፅነት ሲታይ በአብዛሃኛው ተማሪዎች የሚረዱት ነው፡፡ ቢሆንም በምንባቦች ውስጥ ግልፅነት የሌላቸው ቃላት ወይም ቋንቋቸው ግልፅ ያልሆኑ ሀሳቦች በጥናቱ ታይተዋል ፡፡ ስለዚህ ለአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር እንከን ስለሚፈጥሩ ምንባቦቹ እርማት ተደርጉባቸው ቢዘጋጁ፡፡

- የአንብቦ መረዳት ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ሲታዩ 15 ትዕዛዞች መልመጃዎቹ በምን ዓይነት መንገድ መልስ እንደሚመለሱ የሚገልፀት የለም፡፡በቃል ይገለፅ በፅሑፍ የሚያብራሩት የለም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች መልመጃዎችን ለመስራት የትዕዛዞች ሁኔታ ወሳኝ በመሆኑ የመፅሐፍ አዘጋጆች ይህንን ቢያስተካክሉ፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ መምህር ለመሆን ለሚሰለጥኑ አዲስ ሰልጣኞች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚሰጧቸው ስልጠናዎች ስለአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጭምር ማስተማርና ማሰልጠን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም ሰልጣኞቹ ራሳቸው ብልሃቶቹን የመተግበር ብቃት እንዲኖራቸው ተገቢ ትምህርት በመስጠት ብሎም በክሂሎች የማስተማር ስነዘዴዎች ውስጥ የብልሃቶችን አተገባበር ጭምር በማካተት በእውቀትና በክህሎት የተሻሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎችና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ለማንበብ ክሂል መማሪያ ምንባቦችን ሲመርጡና የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ሲያዘጋጁ ብልሃቶችን በግልጽ ማቅረብን እንደአንድ የማንበብ ተግባራት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበት የተሻለ ይሆናል፡፡

## ዋቢ መፃህፍት


ማረው ዓለሙ (2007) ዘመናዊ ያማርኛ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ፣አልታ ፕሪንቲንግ ፕሬስ

በድሉ ዋቅጅራ (2007)፣በሰነ ፅሑፍ ቋንቋን ማሰተማር፡፡ ህትመት ፍር ኢስት ትሬድንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር 0111565352

ተስፋየ ሽዋየ(1986)፣አንብቦ መረዳት እና የመፅሐፍ ችሎታን ማዳበር፡፡ አዲስ አበባ በትምህርት መሣሪያዎች ፣ማምርቻና ማክፋፍያ ድርጅት

ታደሰ ሲባሞ(2007)PGDT432 subgect Area method 11 ለማሰተማሪያነት የተዘጋጅ ሞጅል ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ያልታተመ

ነብዩ ጋሹ (2005) በግጥም አማካኝነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የፅህፍት ችሎታን ማዳበር ፣በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሔደ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ያለታተመ

እመቤት እሸቴ (2011) አንብቦ መረዳት እና የመፃሐፍ ክሂል የይዘት አቀራረብ ትንተና /በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ተተኩኒሪነት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያለታተመ

እሸቴ መብራቴ (2003) የማንበበና የመፃሐፍ ኪሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ኪሂሎችን በማጉለበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረገግጥ የተደርግ ሙከራዊ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ያልታተመ

ያለው እንዳውቅ (2006)፣የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሰቲ ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት ሦሥተኛ እትም፡፡

ደረጀ ገብሬ (2013) መረሔ ንባብ የማንበብ ክሂል ማበልፀጊያ፡፡አደሰ አበባ ዩኒቨርስቴ፣አፍሪካ ማተሚያ+251116461216

ፀጋየ ኃረጋይ (2006) GDT421 subject area method I ለሚለው ት/ት ማሰተማሪያነት የተዘጋጅ ሞጅል ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ያልታትመ

ፍቅሩ ወልደ ኪዳን (2008) የቋንቋ ኪሂሎችን በማቀናጅት አማርኛን ማሰተማር የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማጉልበት ያለው ፋይዳ (አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት )፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ያልታተም

መጋቢው ኃይለማርያም፡፡ (2009 ዓ.ም) ፡፡ በ2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ተነባቢነት ደረጃ (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ሙሉገበያ ያለው። (2009 ዓ.ም) ፡፡ የፅሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

በጎሰው የሺዋስ። (2003 ዓ.ም) ፡፡ የነባርና የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

እንድሪስ አባይ። (2009 ዓ.ም) ፡፡ በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅእኖ (ያልታተመ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ዘውዱ መብሬ። (2008 ዓ.ም)። ሚናለዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋፅኦ (ያልታተመ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት)። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

Alemayehu, B. (2015). *Assessment of reading and writing skills in the 8th-grade Amharic curriculum*.

Anne, T. (2014). *Cognitive strategies for effective reading and writing*.

Bante, M. (2017). *The role of reading and writing proficiency in student development*.

Bell,F.L.and Le balance,L.B(2000). The language of glosses in 1.2 reding on computer :learners preference, Hispania, 83(2),274-285

Chanyalew, A., & Abiy, W. (2015). *Integrating reading and writing skills in language education*.

Cunningsworth, A. (1995). *Choosing Your Coursebook*.

Dereje, G. (2018). *Cultural and linguistic integration in language education*.

Duke, N. K. & Pearson, P. D. (2009). "Effective Practices for Developing Reading Comprehension".

Goshu, Y. (2003). *Impact of reading comprehension on educational achievement*.

Grant, N. (1987). *Making the Most of Your Teaching: A Guide for English Language Teachers*.

Griffiths, C. & Cansiz, M. (2015). "The Importance of Reading Comprehension in Language Learning".

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*.

Joyce ,E,(1997). Which words should be glossed in 1,2 reading materials?A study of first, second and third semester French students recall (report number FL024770).pennsql vania language forem ,(ERIC docment reproduction service No.ED 427508).64-98

Khezrlou, S. (2012). "Reading as a Meaning-Making Process: A Conceptual Framework".

L.Hirschman, M, light ,E. Breck , and J. Burger .1999 Deen Read :Areading comprehensions system. In procedings of the 32th Annual meeting of the association for computational linguistic

Mekabir, D. (2009). *Reading skills and understanding ability: The importance of reading comprehension for learning other subjects*.

Mekonnen, E. (2019). *Effective teaching strategies for reading comprehension*.

Mulugebariya, E. (2009). "Reading Comprehension and Its Importance".

Richards, J. C. (2001). *Curriculum Development in Language Teaching*.

Tekle, S. (2020). *The relationship between reading and writing skills in education*.

Ur, P. (1996). *A Course in Language Teaching: Practice and Theory*.

Yaman, S. & Cakici, D. (2013). "Reading Comprehension: A Fundamental Skill in Learning".

Yussof, M. et al. (2012). "Engaging with Text: Reading Strategies for Better Comprehension".

Zewdu, G. (2008). *Reading and writing as essential skills for academic success*.

## አባሪ አንድ

**የአንብቦ መረዳት ለማስተማር ከቀረቡ ትዕዛዞች መልመጃዎች በምን ሁኔታ እንደሚሰሩ የማይልፁ ትዕዛዝ** ገጽ


- ምንባቡን መሰረት በማድረግ እውነት የሆነውን ትክክል ውሸት----------------- 49
- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የተብራራ መልስ ስጡ -------------79
- ለሚከተሉት ቃለት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ-----------------79
- ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ----------------------------------------------80
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ-------------------------------107
- የሚከተሉትን ጥያቄወች በምንባቡ መሰረት እውነት የሆነውን ትክክል ውሸት የሆነውን ስህተት በማለት መልሱ---------------------------------------------------------135
- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢ ገለፃ ስጡ---------------------136
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ በምንባቡ መሰረት እውነት የሆነውን ትክክል፣ ውሸት የሆነውን ስህተት በማለት መልሱ-----------------------------------------164
- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢ ማብራሪያ ስጡ -----------165
- ለሚከተሉት ጥያቄወች በምንባቡ መሰረትመልስ ስጡ---------------------------186
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ-------------------------------209
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአነበባችሁት ተውኔት መሰረት መልሱ-------------269
- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመንስኤ እና ውጠየት ዓረፍተ ነገር አዋቅሩ--------139
- ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ መንስኤና ውጤት ጥንቅሩን አሳዩ-139
- በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መሰርቱ-----------------------------------------182

## አባሪ ሁለት

**የፅህፈት ክሂል ለማስተማር የመልመጃዎች ትዕዛዝ** **ገጽ**


- ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ ከሦስት አንቀጽ ያላነሰ ድርሰት ፃፉ--19
- የዱር እንስሳት በሚል ርዕስ አስተዋፅኦ ንደፍ----------------------------------------19
- ባህላዊ የህፃናት ጨዋታዎችን ከሚያውቁ ሰዎች በመጠየቅ ባህላዊ ክዋኔውን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ--------------------52
- ከሚከተሉት ረዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ ከሁለት አንቀጽ በላይ አመዛዛኝ ድርሰት ፃፍ-----------------------------------------------------------------------------------54
- በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ከሦስት አንቀጥ በላይ አመዛዛኝ ድርሰት ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ -------------------------------------------------------------------55
- የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሰረት ወደ አሁን ጊዜ ቀይራችሁ ፃፍ-------------------------------------------------------------------------------58
- ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ በመወያየት የተገለፁትን ነጥቦች በማካተት ‹‹የህፃናት መብት›› በሚል ርዕስ ድርሰት ፃፍ-----------------------------------------------191
- የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሚያጋልጡ አምላካች ነገሮች ዙሪያ ከሶስት አንቀፅ ያላነሰ ድርሰት ፃፍ -------------------------------------------------------------------240

## አባሪ ሦስት

### አንብቦ መረዳት እና ፅህፈትን አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ትዕዛዝ ሁኔታ

ገጽ


- ምንባቡን ደጋግማችሁ በማንበብ የቀረበውን ሰንጠረዥ አሟሉ------------------49
- እንቆቅልሽ ከሚያውቁ ሰወች በመጠየቅ ከተረዳችሁ በኋላ ፅፋችሁ በመምጣት ባህላዊ ክያኔውን በጠበቁ መልኩ በክፍል ውስጥ አቅርቡ----------------------------------69
- ከመፅሃፍ በማንበብ አምስት ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመፃፍ ስለ አጠቃቀማቸው ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ--------------------------------------------------------70
- ንባቡን ደጋግማችሁ በማንበብ የክልልላችን የህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያሳይ ግራፍ ስሩ--------------------------------------------------------------------------------137
- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተገቢ ማብረራሪያ ስጡ------------139
- ከላይ በምሳሌ ባያችሁት ድርሰት መሰረት በሚከተሉት ርዕስ ጉዳዮች ከአራት አንቀፅ ያላነሰ ገላጭ ድርሰት ፃፍ---------------------------------------------------------169
- ከሚከተሉት ረዕሰ ጉዳዮች መፅ ሃፍ በማንበብ እና የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ በማሰባሰብ አጠናክራችሁ ድርሰት ፃፍ----------------------------------192
- ቀጥሎ የቀረበውን የሽማኞች ማህበር የሚል ፅሁፍ መንደርደሪያ አድርጋችሁ ከተወያያችሁ ነኋላ በጋር የደረሳችሁበትን ስምምነት በቃለ ጉባኤ አስደግፋችሁ ግለጹ----232
- ከላይ በምሳሌ የቀረበውን ንባብ አመዛዛኝ ድርሰት ያሰኘውን ዘርዝራችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ--------------------------------------------------------------------------56

## አባሪ አራት

### አንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የቋንቋ ግልፅነት የሌላቸው ቃላት

| ስህተት ቃላት | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | ተለምዶዎ | 27 |
| 2. | የሚንቀሱና | 27 |
| 3. | ገበሎ | 107 |
| 4. | አታወቅም | 107 |
| 5. | ብለፅግና | 107 |
| 6. | የሚበቅቱኝ | 262 |
| 7. | የሚፈትሩን | 262 |
| 8. | ያምቡልልዎት | 264 |
| 9. | ሽረዎት | 265 |
| 10. | ስሽናክል | 266 |
| 11. | ጭዳ | 267 |
| 12. | ያሚቧረወቁት | 267 |
| 13. | እንዷን | 268 |
| 14. | ልዩበት | 207 |

## አባሪ አምስት

ለመምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆች

1. የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ የተማሪው መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የፅሕፈት ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ምንባቦች የቋንቋ ግልጽነት እና የሀሳብ አሻሚነት ሁኔታ እንዴት አያችሁት?
2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና ለፅሕፈት ክሂል ትኩረት የመስጠት ሁኔታ ምን ይመስላል፡፡ በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና የፅሕፈት ክሂል ትኩረት በተመለከተ
3. በ8ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት እና ለጽህፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማቅረብ በመማር ማስተማሩ ምን ምን ዘዴዎችን ትጠቀማላችሁ? አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅትና የማስተማሪያ ዘዴዎች
4. በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተማሪ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አዋህዶ ለማቅረብ መልመጃዎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ሁኔታ ምን ይመስላል? የአንብቦ መረዳት እና የፅሕፈት ክሂል ቅንጅት በተመለከተ
5. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ከተማሪው ህይወት ጋር ያላቸው ተያያዥነት በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል እና ለገሃዱ ዓለም ጋር ያለው ቅንጅት
6. በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት እና የጽሕፈት ክሂል ለማስተማር መልመጃዎችን ለመስራት የትዕዛዞችን ግልጽነት እንዴት ነው? አንብቦ መረዳና የጽሕፈት ክሂል የተመለከቱ ጥያቄዎች ትዕዛዞች ግልጽነት በተመለከተ